ወርኃዊ ጥንቅር፣ ቁ. 010
ሕዳር 2018 ዓ.ም



# የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ክራሞት

እንደራሴ

እንደራሴ በብርጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።

research@bridge-et.org

BRIDGE Research & Innovation-
Parliaments. Peace. Policy

## መልክዓ-ብሪጅ

መቀመጫውን አዲስ አበባ ያደረገ፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ዐዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሰረት አገር በቀል የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ሆኖ የተመዘገበ የጥናትና ምርምር ተቋም ነው። ብሪጅ፣ በዋናነት በኢትዮጵያ እና በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) አባል አገራት ውስጥ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እንዲጎለብት እና ሰላም እንዲበለጽግ የሚሠራ ገለልተኛ እና ለትርፍ ያልተቋቋመ ፖሊሲ ተኮር የጥናት እና ምርምር ተቋም ነው።

## ተልዕኮ

ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ይጎለብት ዘንድ፣ ለፖሊሲ አወጣጥ ግብዓት የሚሆኑ፣ ተጨባጭነት ያላቸው ምርምሮችን ማድረግ እና የፖሊሲ ምክረ ሐሳቦችን ማቅረብ፤

## ርዕይ

በሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች እና በቀጠናዊ የሰላም፣ ዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰዋዊ እና ቁሳዊ ልማት ላይ፣ በኢጋድ ቀጠና ተቀዳሚ የምርምር እና ፖሊሲ አመንጪ ማዕከል መሆን፤

## መሠረታዊ ዕሴቶች

- አጽንዖተ ትኩረት፦ ከፍተኛ ትኩረት የተሰሩ እና ተጨባጭነት ያላቸው ጥናት ምርምሮችን ማቅረብ፡፡
- አዲስነት፦ ለዲሞክራሲያዊ አሥተዳደር እና ሰላም ተግዳሮቶች ፈጠራዊ እና ተለዋዋጭ መፍትሔዎች የታከለባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ማዋጣት
- ታማኝነት፦ ተዓማኒነት ያላቸውን የምርምር ውጤቶችን በማቅረብ ተዓማኒነትን መጠበቅ

## ግቦች

ኢትዮጵያ እና በኢጋድ ቀጠና የሚገኙ የፌዴራል እና የክልል ፓርላማዎች በሚከተሉት መንገዶች ማጠናከር

- ተጨባጭ ምርምሮችን መከወን
- የእንደራሴዎችን ብቃት ለማሳደግ የዐቅም ግንባታ ድጋፎችን ማድረግ
- ተጠያቂነትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሕዝብ ተወካይ ምክር ቤቶች ክንውኖችን መከታተል

+251 911 86 12 34

+251 115 57 74 96

research@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.

# ማውጫ

1. 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን ........ 2

2. የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት ........ 3

2.1 የጸደቀው ሕግ ........ 3

2.2 ረቂቅ ሕግጋት ........ 4

2.3 አስረጂ መድረኮች ........ 5

3. የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር ........ 7

3.1 የተቋማት ሪፖርቶች ........ 7

3.2 የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶች ........ 14

3.2.1 የተቋማቱ ጉብኝቶች ........ 14

3.2.2 የመስክ ጉብኝቶች ........ 19

4. የውክልና ሥራ ........ 22

5. የፓርላማ ዲፕሎማሲ ........ 22

6. እንደራሴዎቹ ስለ'ራሳቸው ........ 24

7. ኢትዮጵያ ምን ተስማማች? ........ 26

8. ጎዳና ሲታጠን ........ 27

9. ሹመቶች ........ 27

10. የብሪጅ አጭር ዳሰሳ፦ በብሔር ብሔረ ሰቦች በዓለ ቀን እና ባሻገር ዙሪያ ........ 28

ስያሜዎቹ ሲታወሱ ........ 29

ፖለቲካ እና ባህል ........ 30

ቀኑ እና ምክር ቤቱ ........ 31

የበዓሉ መሠረት ........ 32

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ በወርኀ ኅዳር የተለያዩ ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነቶቹን ከውኗል። ከእነዚኽ ዋንኛ ኃላፊነቶቹ መካከልም፣ ሕግ ማውጣት፣ የሥራ አሥፈፃሚ ተቋማት ሪፖርቶችን ማድመጥ እና የፌደራል ተቋማትን መጎብኘት፣ የውክልና ሥራ፤ እና የፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ ሥራ የሚጠቀሱት የወሩ የምክር ቤቱ አበይት ክንውኖቹ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም፣ ምክር ቤቱ የራሱን የሦሥት ወራት ሥራ አፈፃፀም ጨምሮ፣ ለእንደራሴዎቹም የዐቅም ማጎልበቻ ሥልጠና እንዲሰጥ ሲያደርግ፣ የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት የጸደቀበት ታላቅ ቀን እንደሆነ የሚታመነውን ኅዳር 29ን ዘክሯል። ይኽች የብሪጅ ዐሥረኛ ዕትምም፣ እኒህን የምክር ቤቱን የኅዳር ክራሞት ጨምሮ፣ የብሔር ብሔረ ሰቦች ሉዓላዊነትን የሚነግረውን ቀን እና ከቀኑ ባሻገር ባሉ ርዕሰ-ጉዳዮች ዙሪያ አጭር ዳሰሳዋን አካታ ቀርባለች።

## 1. 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን

| 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 5ኛ ዓመት የሥራ ዘመን | ቀን | አጀንዳዎች |
|---|---|---|
| **3ኛ መደበኛ ስብሰባ** | ኅዳር 25 | * የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር ዐዋጅ ለማሻሻል የቀረበ ረቂቅ ዐዋጅ ቁጥር 1397/2018ን ማጽደቅ፤<br>* ሹመቶችን ማጽደቅ፤<br>* የተለያዩ የብድር ስምምነቶችን ማጽደቅ፤ |

## 2. የምክር ቤቱ ሕግ የማውጣት ተግባራት

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በወርኃ ኅዳር የቀረበለትን አንድ ማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጅን ሲያጸድቅ፣ አራት ረቂቅ ዐዋጆችን ደግሞ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መርቷል።

### 2.1 የጸደቀው ሕግ

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በወርኃ ኅዳር ያጸደቀው ብቸኛ ሕግ፣ **የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎችን አስመልክቶ የቀረበለትን የማሻሻያ ረቂቅ ዐዋጅ** ነበር። ምንም እንኳን ይኽ ዐዋጅ፣ በቀደመው ሐምሌ ወር ላይ ጸድቆ የነበረ ቢሆንም፣ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ለእንደራሴዎቹ ያስገባውን ቅሬታ ተከትሎ ማሻሻያውን አጽድቋል። እንደ ምክር ቤቱ መረጃ ከሆነም፣ የተሻሻለው ዐዋጅ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከዕጩዎች ምዝገባ ጋር በማያያዝ የሚያሰሙትን ቅሬታ በመፍታት እና ጥያቄውን በመመለስ ለሰባተኛው ዙር ጠቅላላ ምርጫ አስቻይ ሁኔታ ለመፍጠር እንደሚያስችል ተጠቁሟል። የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ የማሻሻያ አዋጁን አስመልክቶ ባቀረቡት ማብራሪያ፣ በየደረጃው በሚደረጉ ሁሉን ዓቀፍ ምርጫዎች በአኩልነት እና በነጻነት የማሳተፍ መብትን ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን አንስተዋል። ከዚህ አኳያ የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ-ምግባር ዐዋጅ ጸድቆ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑንም አክለው ማስታወሳቸው ተዘግቧል።



*የተከበሩ አፈ-ጉባኤ ታገሰ ጫፎ፣ በውይይቱ ወቅት፤*

በዚኽ ዐዋጅ መሰረት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለሕዝብ ተወካዮች እና ለክልል ምክር ቤቶች ለሚያቀርቧቸው እያንዳንዱ ዕጩዎች የድጋፍ ፊርማ እንዲያቀርቡ ተደንግጓል። ይሁንና የድጋፍ ፊርማ ጥያቄው በስድስተኛው ዙር አገራዊ ምርጫ ወቅት በተከሰተው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ተፈጻሚ እንዳይሆን ታግዶ እንደነበርም አፈ ጉባኤው አስታውሰዋል። የድጋፍ ፊርማ ጥያቄው በሰባተኛው ዙር አገራዊ ምርጫ ተግባራዊ እንዲሆን ማሻሻያ ተደርጎበት የጸደቀ ቢሆንም፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከቅድመ-ዝግጅት ምርጫው እስከሚካሄድበት ጊዜ ድረስ የሚሰሩ በርካታ ሥራዎች በመኖራቸው እና በቂ ጊዜ ስለሌለ የድጋፍ ፊርማ ለማሰባሰብ እንደሚቸገሩ መግለጻቸውን የተከበሩ ታገሰ በዚያ የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ አንስተዋል።

እንደ አፈ-ጉባኤው ማብራሪያ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ በሰባተኛው ዙር አገራዊ ምርጫ እንዲሳተፉ አስቻይ ሁኔታ ለመፍጠር የድጋፍ ፊርማውን አስመልክቶ የተቀመጠው አንቀጽ እንዲሻሻል ተደርጓል። በተሻሻለው ዐዋጅ መሰረት በሰባተኛው ዙር አገራዊ ምርጫ የሚሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች የዕጩዎች የድጋፍ ፊርማ አይሰበስቡምም ብለዋል። በዐዋጁ አንቀጽ ተቀምጦ የነበረው የፖለቲካ ፓርቲዎች የዕጩዎች ድጋፍ ማሰባሰብ ፊርማ እንዲቀር መደረጉ አሳታፊ እና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድ

እንደሚያስችልም ገልጸዋል። ይህ ዐዋጅም፣ ቀደም ሲል የጸደቀውን ዐዋጅ ቁጥር 1162/2014 አንቀጽ 32(2) እና አዲስ የተጨመረውን ንዑስ አንቀጽ 8 ከሥራ ውጪ ያደርጋል ተብሏል። እንደራሴዎቹም፣ የማሻሻያ ዐዋጁን ደግፈው፣ አገሪቱን ተጠቃሚ ለማድረግ ታስቦ የተዘጋጀ በመሆኑ ተገቢ እና ትክክለኛ ማሻሻያ ነው ማለታቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷቸዋል። እንደራሴዎቹም፣ ይኽንኑ ረቂቅ ማሻሻያ ዐዋጅ፣ **ዐዋጅ ቁጥር** 1397/2018 ሲሉ በሙሉ ድምጽ አጽደቀውታል።

## 2.2 ረቂቅ ሕግጋት

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ሸፋን በሰጠነው ኅዳር ወር ውስጥ ባካሄደው አንድ መደበኛ ስብሰባው፣ አራት ረቂቅ ዐዋጆችን ይመለከተዋል ላለው ቋሚ ኮሚቴ መርቷል።

ምክር ቤቱ በቀዳሚነት የተመለከተው ረቂቅ ዐዋጅ፣ **በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሕዝባዊት ሪፐብሊክ ቻይና መንግሥት መካከል የተደረገውን የወንጀል ጉዳዮች የጋራ የሕግ ትብብር ስምምነትን** ነበር። በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር የሆኑት የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ የረቂቅ ዐዋጁን አስፈላጊነት ሲያብራሩም፣ የኹለቱ አገራት ኹለንተናዊ ግንኙነት እያደገ በመምጣቱ፣ ዜጎች እዚያም እዚህም ወንጀል ፈጽመው ለመሰወር የሚያደርጉትን ሙከራ ለማስቀረት እና አሳልፎ የመስጠት ግዴታዎችን ያካተተ መሆኑን ለእንደራሴዎቹ አብራርተውላቸዋል። እንደራሴዎቹም ረቂቅ ዐዋጁን፣ **ዐዋጅ ቀጥር** 1/2018 በማድረግ ለዝርዝር ዕይታ ለሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርተውታል።

በዚኹ ዕለት ምክር ቤቱ ሊመለከተው የፈቀደው ረቂቅ ዐዋጅ፣ **በኢትዮጵያ እና ቻይና መንግሥት መካከል የተደረገውን፤ የፍርደኞችን ማስተላለፍ ስምምነት ረቂቅ ዐዋጅን** ነበር። በዚኹ ረቂቅ ዐዋጅም ላይ ማብራሪያ የሰጡት የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ ሲሆኑ፤ ‘ርሳቸውም፣ ረቂቅ ዐዋጁ የኹለቱ አገራት ፍርደኞች በ‘የአገራቸው ተዘዋውረው የፍርድ ጊዜያቸውን እንዲጨርሱ እና ወደ ማኅበረሰባቸው ተቀላቅለው አምራች ዜጋ እንዲሆኑ የሚያግዝ ነው ብለዋል ተብሏል። እንደራሴዎቹም፣ ረቂቁን ዐዋጅ፣ **ዐዋጅ ቁጥር** 2/2018 በማድረግ ለሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርተውታል።



*በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር የሆኑት የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ የረቂቅ ዐዋጆቹን አስፈላጊነት ሲያብራሩ፤*

ኅዳር 25 በዋለው የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ፣ እንደራሴዎቹ ወደ ሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የመሩት ሌላይኛው ረቂቅ ዐዋጅ፣ **በኢትዮጵያ እና በብራዚል መንግሥታት መካከል፣ ፍርደኞችን ስለማስተላለፍ የሚያትተውን ስምምነት** ነበር። ይኽንኑ ረቂቅም፣ **ዐዋጅ ቁጥር** 3/2018 አድርጎ ለዝርዝር ዕይታ ወደ ቋሚ ኮሚቴ ሲመራ፤ በተመሳሳይም፣ **በኢትዮጵያ እና በደቡብ አፍሪካ ሪፐብሊካን መንግሥታት መካከል የተደረገውን እና በወንጀል ጉዳይ የሚፈልጉ ሰዎችን የአሳልፎ መስጠት ስምምነት ረቂቅ ዐዋጅንም፤ ዐዋጅ ቁጥር** 4 /2018 ሲል ለዚያው የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መምራቱን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ያሳያል።

## 2.3 አስረጂ መድረኮች

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች በኅዳር ወር በጊዜ ምጣኔ በቀዳሚነት የከወኑት የአስረጂ መድረክ፣ **በሥነ-ምኅዳር አገልግሎት ክፍያ** ዙሪያ የተዘጋጀውን ረቂቅ ዐዋጅ አስመልክቶ ነበር። በዚኽ የአስረጂ መድረክ ላይ የተገኙት፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውኃ፣ መስኖ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዋ የተከበሩ ወ/ሮ ፈቲያ አህመድ፣ ዐዋጁ አዲስ እና ንዑስ-ኢኮኖሚ ዘለል ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ተቋሙ እስከ ክልል ድረስ በየደረጃው ላሉ ክፍለ-ኢኮኖሚዎች ግንዛቤውን የማስፋት ሥራ መሥራት እንዳለበት አሳስበዋል። ሰብሳቢዋ አክለውም፣ ከሥርዓት-ምኅዳሩ ተጠቃሚ በሆኑ እና ባልሆኑ አካላት መካከል ግጭት እንዳይፈጠር ፕላት ፎርም መዘጋጀት እንዳለበትም ጠቁመዋል። የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም አለማየሁ በበኩላቸው፣ ዐዋጁ አካባቢን ከመንከባከብ እና ጠብቆ ከማቆየት ባሻገር ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑን ገልፀው፣ እንደዚህ አይነት ለአገር ጠቃሚ የሆኑ ሥርዓቶችን መዘርጋቱ የሚበረታታ ተግባር መሆኑን አንስተዋል ተብሏል።

የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተሯ ኢንጂነር ሌሊሴ ነሜ በበኩላቸው፣ ዐዋጁ አገሪቱ አሁን የያዘችውን የአረንጓዴ ልማት ጉዞ እንዲኹም የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎችን ትኩረት ሰጥቶ ለመሥራት የሚያግዝ እንደሆነ ማብራራታቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷል፡፡ ሥርዓት በመዘርጋቱም ከዓለም ዓቀፉ የአየር ንብረት ለውጥ ፈንድ ተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንድናገኝ ያግዛል ያሉት ዋና ዳይሬክተሯ፣ ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማበረታታትም ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ገልፀዋል ተብሏል።



*በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የውኃ፣ መስኖ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዋ የተከበሩ ወ/ሮ ፈቲያ አህመድ በአስረጂ መድረኩ ላይ፤*

ከኹለት ሳምንታት በኋላ በዚኹ ረቂቅ ዐዋጅ ዙሪያ በተካሄደ ሌላ መድረክ ላይ የተገኙት፣ በምክር ቤቱ የውኃ፣ መስኖ ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. አወቀ አምዛዬ፣ ረቂቅ ዐዋጁ የአገርን የሥነ-ምኅዳር ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም የሚረዳ ነው ብለዋል ተብሏል። ከዚኽ በተጨማሪም ምክትል ሰብሳቢው፣ ከክፍያ ሥርዓት ጋር በተያያዘ የተቀመጠው በጥቅል በመሆኑ አፈፃፀም ላይ ተግዳሮቶችን እንዳይፈጥር በግልፅ ማስቀመጥ ያስፈልጋል ሲሉ አስገንዝበዋል። በምክር ቤቱ የፕላን በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ በተራቸው፣ ትርጉም እና የተፈፃሚነት ወሰን ጋር በተያያዘ ማረም እንደሚያስፈልግ እና አሻሚነት ያላቸውን አገላለጾችንም ማስተካከል ይገባል ሲሉ ማሳሰባቸውን መረጃው ጠቅሷል።



*በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ሰላሞን ላሌ፤*

ኅዳር 17 2018 ዓ.ም. የተካሄደው ኹለተኛው የአስረጂ መድረክ ደግሞ፣ **በየዕፅዋት ጥበቃ እና ኳራንታይን ረቂቅ ዐዋጅ** ዙሪያ ሲሆን፣ መድረኩ የተካሄደው በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ሰላሞን ላሌ፣ አሁን ዘመኑ ከደረሰበት ደረጃ እና በዕፅዋት እና በብዝሓ ሕይወት ላይ ከሚደርሰው ጉዳት አንፃር፣ ከዚኽ በፊት የነበረው የሕግ ማዕቀፍ ሊያሰራ ባለመቻሉ ይኽንን ዐዋጅ ማውጣት እንዳስፈለገ መናገራቸው ተሰምቷል። ከዚኽ ባለፈም፣ የግብርና ዘርፋን ለማሻገር እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ምርትን የሚያበላሹ የዕፅዋት ተባዮችን መከላከል ያስፈልጋል ያሉት ሰብሳቢው፣ ይኽንን ተግባራዊ ለማድረግም ረቂቅ ዐዋጁ ከፍተኛ ፋይዳ እንደሚኖረው ጠቅሰዋል። የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታው ዶ.ር. መለስ መኮንን በበኩላቸው፣ ረቂቅ ዐዋጁ ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶችን ዓይነት፣ መጠን እና ጥራት ለማሳደግ እና ደኅንነታቸውን ለማስጠበቅ ፋይዳው የጎላ መሆኑን መናገራቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷቸዋል።

## 3. የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር

የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደራሴዎች፣ ከዋና ዋና ሥራዎቻቸው አንዱ የሆነው የአሥፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር ሲሆን፤ በዚኽ ረገድም፣ በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ወርኃ ኅዳር የዐሥራ አምስት የአሥፈጻሚ ተቋማትን ሪፖርቶች አድምጠዋል፤ ከምክር ቤቱ ወጣ ብለውም የተለያዩ ተቋማትን በ'የኮሚቴዎቻቸው አማካኝነት በአካል ሲመለከቱ፣ በዛ ያሉ የመስክ ጉብኝቶችንም ከውነዋል።

### 3.1 የተቋማት ሪፖርቶች

የተለያዩ የፌዴራሉ የመንግስት ተቋማት፣ ተጠሪ ለሆኑባቸው የተለያዩ የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎች፣ የ2018 ዓ.ም. ሩብ ዓመት የሥራ አፈፃፀማቸውን ሪፖርት በወርኃ ኅዳርም ሲያቀርቡ፣ ምክር ቤቱም ከዚህ አለፍ ብሎ የአንዳንድ ተቋማትን ግብረ-መልሶችም አድምጧል።

በወሩ መጀመሪያ የባጀት ዓመቱን የሦሥት ወራት አፈጻጸሙን ያቀረበው **የሴቶች እና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር** መሥሪያ ቤት ሲሆን፣ ሚኒስትራ ዶ.ር. ኤርጎጌ ተስፋዬ የተቋማቸውን ሪፖርት፣ ለምክር ቤቱ የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አቅርበዋል። በሰላም ግንባታ እና በግጭት አፈታት ዙሪያ የሴቶችን ተሳትፎ የማሳደግ ሥራዎችን መሥራታቸውን የገለጹት ሚኒስትሯ፣ ለሴቶች እና ለወጣቶች የሥራ ዕድል በመፍጠር የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን ማስደግ መቻሉንም ጨምረው አንስተዋል።

የሴቶች እና የሕፃናትን ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ የማሻሻያ ሥራዎችን ለማሳለጥ የአሠራር ማዕቀፎችን እና ሰነድ በማዘጋጀት እንዲኹም ቅንጅታዊ አሠራርን በማጠናከር ከተለያዩ አገር በቀል እና የውጭ ድርጅቶች ጋር በጋራ በመሥራት በተደረጉ ድጋፎች ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረግ እንደተቻለም ዶ.ር. ኤርጎጌ ገልፀዋል ተብሏል። ቋሚ ኮሚቴው እያደረገ ያለው ክትትል እና ድጋፍ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አቅም የሚፈጥር እንደሆነም የጠቀሱት ሚኒስትሯ፣ እንደአገር የሱስ ማገገሚያ ማዕከል ከችግሩ ስፋት አንፃር ውስንነት በመኖሩ ሁሉም አጋር አካል የማኅበረሰቡ ችግር የእኛም ችግር ነው ብለው ማዕከላትን ከማስፋፋት አንፃር ሊሰሩ እንደሚገባ ተናግረዋል ተብሏል፡ ፡ የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ታደለ ቡራቃ በበኩላቸው፣ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረግ ባሻገር፣ በገጠር የሚገኙ ሴቶች የመሬት ባለቤትነታቸው እንዲረጋገጥ የተሰሩ ሥራዎችን በጥንካሬ እንደሚታዩ መጠቀሳቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።



*የሴቶች እና ማኅበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴር ሚኒስትራ ዶ.ር. ኤርጎጌ ተስፋዬ ሪፖርታቸውን ሲያቀርቡ፤*

በዚያው ኅዳር ወር መግቢያ ላይ፣ የሦሥት ወራት ሪፖርቱን ያቀረብ ዘንድ የተጠራው **የባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር** ሲሆን፣ የተቋሙን ሪፖርት ያደመጠውም የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ታደለ ቡራቃ፣ የተቋሙ የሩብ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም አማካይ አፈጻጸም 99.3 በመቶ መሆኑን በጥንካሬ አንስተዋል ተብሏል፡፡ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በማኅበራዊ ዘርፍ በሩብ ዓመቱ ካከናወናቸው ተግባራት

አንፃር አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ ተጋላጭ ሴቶች እና ሕፃናት ከተሳታፊነት እና ከተጠቃሚነት አንጻር የሕግ ማዕቀፎች ፀድቀው ወደ ሥራ ሊገቡ እንደሚገባ አሳስበዋል ተብሏል። ሰብሳቢው አክለውም፣ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን ከመከላከል ባሻገር ከስደት ተመላሽ ለሆኑ ዜጎች የማቋቋም የሥነ-ልቦና እና ማኅበራዊ አገልግሎት ድጋፉ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበትም ጠቁመዋል።

የባህል እና ስፖርት ሚኒስትሯ ክብርት ወይዘሮ ሸዊት ሻንካ በሪፖርታቸው፣ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የአፍሪካ የባህል ስፖርት አባል አገር ከመሆን አልፋ የምክትል ፕሬዝዳንትነት ቦታ ያገኘችበት ዓመት መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል። ከዚኽም በተጨማሪ፣ የኢትዮጵያን ባህል ለማስተዋወቅ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በትኩረት እየሠራ በመሆኑ፣ የውጭ አገር ቱሪስቶች ፍሰት እየጨመረ መሆኑን ጠቁመው፤ የኢትዮጵያን ባህል ወደ ውጭ በመውሰድ የማስተዋወቅ ሥራ መጀመራቸውንም ለቋሚ ኮሚቴው አባላት አስረድተዋል፡፡



*የባህል እና ስፖርት ሚኒስትሯ ክብርት ወይዘሮ ሸዊት ሻንካ ሪፖርታቸውን ሲያቀርቡ፤*

በዕለተ-ኅዳር ሠሥት የዚኽን ሩብ ባጀት ዓመት ሪፖርት ለማቅረብ የተጠራው የፌደራሉ ተቋም **የጤና ሚኒስቴር** ሲሆን፤ በምክር ቤቱ የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴም ሪፖርቱን አድምጧል።

ሪፖርቱን ያቀረቡት ሚኒስትሯ ዶ.ር. መቅደስ ዳባ፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸው በ2018 ዓ.ም የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ለመሥራት ካቀዳቸው ተግባራት መካከል 89 በመቶ የሚሆነውን መፈጸም መቻሉን ሲናገሩ ተደምጠዋል። በሩብ ዓመቱ የእናቶችን የሥነ-ተዋልዶ ጤና ለማሻሻል በተሰሩ ሥራዎች በአገር አቀፍ ደረጃ በጤና ተቋማት ክትትል የሚያደርጉ እናቶች ቁጥር ከነበረበት 37 በመቶ ወደ 41 በመቶ ማሳደግ መቻሉንም ሚኒስትሯ ተናግረዋል። የኮሌራ እና የኩፍኝ ወረርሽኞችን ለመቆጣጠር በተሰሩ ሥራዎች በበሽታዎቹ የሚመጡ ሞቶችን መቀነስ መቻሉን የጠቀሱት ሚኒስትሯ፣ በማኅበረሰብ ዓቀፍ የጤና መድኅን ሽፋን 63 ሚሊየን ዜጎች ተጠቃሚ መሆናቸውን መናገራቸው ተዘግቧል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ታደለ ቡራቃም፣ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከል ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር የሚደረገው ቅንጂታዊ ሥራ መጠናከር እንዳለበት ጠቁመው፤ የኦዲት ግኝቶችን በተመለከተም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተከታትሎ ውጤቱን እስከ ታኅሣሥ 30/2018 ዓ.ም. ድረስ እንዲያሳውቅም አሳስበዋል ተብሏል።



*የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትሯ ዶ.ር. መቅደስ ዳባ ሪፖርታቸውን ባቀረቡበት ወቅት፤*

የወሩ ሌላይኛው ሪፖርት አቅራቢ የነበረው **የግብርና ሚኒስቴር** ሲሆን፣ የሚኒስቴር ተቋሙን እና የተጠሪ ተቋማቱን ሪፖርት ያቀረቡት ሚኒስትሩ አዲሱ አረጋ እንደነበሩም መረጃው ጠቅሷል። ሚኒስትር አዲሱም፣ የእንስሳት ሀብት ልማትን የማዘመን ሥራ፣ ወጣቱን እና ባለሀብቱን በግብርናው ዘርፍ በስፋት በማሳተፍ እየተሰራ መሆኑን በሪፖርታቸው አመላክተዋል ተብሏል። ከዚያ በተጨማሪም፣ አሲዳማ መሬትን በማከም ወደ ሥራ እንዲገባ በባጀት ዓመቱ ከተያዙት አንኳር እቅዶች መካከል አንዱ እንደሆነም፣ በምክር ቤቱ የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አስረድተዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ሰለሞን ላሌ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያን ለማበልፀግ የግብርና ዘርፉ ላይ ሽግግር ማድረግ መሠረታዊ ጉዳይ እንደሆነ እና የግብርና ሜካናይዜሽንን መጠቀም እንደሚያስፈልግም ገልፀዋል ተብሏል። ሰብሳቢው አክለውም፣ የግብርና ትራንስፎርሜሽንን ለማሳካት ማዳበሪያ እና የምርጥ ዘር ግብዓቶችን ማሟላት እንደሚገባ ጠቅሰው፣ የመረጃ አያያዝን በማዘመን ለእርሻ ሊሆን የሚችል የመሬት ምጣኔ ማወቅ እና አሁን እየታረሰ ያለውን የመሬት መጠን በመተንተን በየአካባቢው ያለውን ፀጋ በአግባቡ መጠቀም እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል። በዚኽ ብቻ ያላበቁት ሰብሳቢው፣ የግብርናው ዘርፍ የአገሪቱ የውስጥ እና የውጭ ንግድ ገቢ ምንጭ እንደመሆኑ መጠን፣ የቡና እና ቅመማ ቅመም ምርትን ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ብዛቱ ላይ ብቻ ሳይሆን፣ በዓለም ገበያ ውስጥ ያለውን ተመራጭነት ከፍ ለማድረግ ጥራቱ ላይም በትኩረት መሥራት እንደሚገባ አሳስበዋል ተብሏል። ሌሎቹ የቋሚ ኮሚቴው አባላት በበኩላቸው፣ በሩብ ዓመቱ የእርሻ መሬት፣ የኩታ ገጠም ሜካናይዜሽን እና የሌማት ትሩፋት ሥራው የተሻለ አፈጻጸም ያለው ቢሆንም፣ ከአገራዊ ፍላጎት አኳያ አሁንም በትኩረት መሰራት እንደሚጠይቅ መጥቀሳቸውን መረጃው ያሳያል።



*የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትሩ አዲሱ አረጋ የሩብ ዓመት የተቋማቸውን ሪፖርት ሲያቀርቡ፤*

**የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ**፣ ለአገር ኢኮኖሚ ዕድገት እያደረገ ያለውን አስተዋጽዖ ማጠናከር እንዳለበት የተነገረበት ደግሞ፣ ተቋሙ የሩብ ዓመቱን አፈጻጸም ሪፖርት ያቀረበበት ሌላይኛው የሥራ አሥፈጻሚ ቁጥጥር ኹነት ነበር። በምክር ቤቱ የመንግስት ልማት ድርጅት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ መለሰ መና፣ የዜጎች ተስፋ የመንግስት ልማት ድርጅት እንደመሆኑ መጠን የሚጠበቅበትን ውጤት ማምጣት እንዳለበት አሳስበዋል ተብሏል። በለውጡ መሰረት ተቋሙ ራሱን እያሳደገ መሆኑን የገለፁት የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ኢንጂነር ስለሺ ኮሬም፣ ትርፋማ እና ተደራሽ ከመሆን አንፃር ውጤታማ ሥራዎችን መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ አመላክተዋል።

የቋሚ ኮሚቴው አባላት የተለያዩ ጥያቄዎችን ያቀረቡ ሲሆን፣ የተቋሙ ምክትል ዋና ሥራ አሥፈፃሚ አቶ ሀብታሙ ኃ/ሚካኤል፣ ምንም እንኳን ተቋማቱ ለትርፍ የተቋቋሙ ቢሆኑም ለሚሰጡት አገልግሎት የሚጠበቅባቸው ትርፍ፣ የዐብይ ኢኮኖሚውን ማሻሻያ ተከትለው እና ወጪያቸውን ባማከለ መልኩ እየታየ የሚሰራው መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል። አክለውም፣ ዝቅተኛ አፈጻጸም ያስመዘገቡ የልማት ድርጅቶችን በሚመለከት የሚያስፈልጋቸው የፋይናንስ እገዛ እንዲደረግላቸው ሲሉ የቋሚ ኮሚቴውን አባላት ጠይቀዋል ተብሏል።



*የመንግስት ልማት ድርጅት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ መለሰ መና፤*

ኅዳር የመጀመሪያው ሳምንት መገባደጂያ ላይ፣ የዓመቱን የሦሥት ወራት አፈጻጸሙን በምክር ቤቱ ለሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበው **ትምህርት ሚኒስቴር** ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል እያደረገ ባለው ጥረት ተስፋ ሰጪ ውጤት መታየት ጀምሯል ብለዋል፡፡ በመንግሥት እና በግል ትምህርት ቤቶች መካከል የሚታየውን የትምህርት ጥራት ልዩነት ለማሻሻል ከግብዓት፣ የትምህርት ጥራት እንዲኹም የደረጃ ልዩነት ፍትሓዊ ለማድረግ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከአጋር አካላት ጋር በትኩረት ሊሰራ እንደሚገባም ዶ.ር. ነገሪ ጠቁመዋል፡፡ የትምህርት ሚኒስትሩ ፕ/ር ብርሃኑ ነጋ በበኩላቸው፣ የትምህርት ጥራት ችግርን ለመቅረፍ በትምህርት ማሻሻያው መሠረት መምህራን በሚያስተምሩት የትምህርት ዘርፍ ሰልጥነው ባስመዘገቡት ውጤት ተለይቶ የማበረታቻ ሥርዓት ሊተገበር እንደሚገባ አብራርተዋል ተብሏል፡፡ ከግብዓት አቅርቦት አንፃርም፣ በአዲሱ የትምህርት ሥርዓት ትግበራ ለኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከ105 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጭ ተደርጎ፣ 68.2 ሚሊየን የመማሪያ እና ማስተማሪያ መጻሕፍት ታትሞ አንድ ለአንድ የተዳረሰ መሆኑን በሪፖርታቸው የጠቀሱት ፕሮፌሰሩ፣ ለአንደኛ እና ቅድመ አንደኛ ደረጃ ተማሪዎች የመጻሕፍት አቅርቦት ችግርን ለመፍታት ከክልሎች ጋር በትብብር እየተሰራ መሆኑንም ገልጸዋል ተብሏል።



*የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ፤*

በዚኹ ወር፣ እንደሌሎቹ ተቋማት ኹሉ የሩብ ዓመት ሪፖርቱን እንዲያቀርብ የተጠራው **የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር** ሲሆን፤ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የኢንዱስትሪ እና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዋ ዶ.ር. አማረች በካሎ፣ መሥሪያ ቤቱ ትልልቅ ሥራዎችን እየሰራ እንደሆነ ተናገረው፤ የኢንዱስትሪው ዘርፍ በባህሪው በአንድ ተቋም ብቻ የሚሰራ ሳይሆን ሌሎች ተቋማትን በማቀናጀት መሥራት ያለበት እንደሆነ ማሳሰቢያ ያሉትን ሰጥተዋል ተብሏል። ሰብሳቢዋ፣ የቆዳ ምርትን በዘመናዊ መንገድ ለማሳደግ፣ ዘመኑን የሚመጥን እና የረቀቀ ቴክኖሎጂ እንደሚያስፈልግም አስረድተዋል፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚንስትሩ የተከበሩ መላኩ አለበል፣ ተቋማቸው የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን እና ቴክኖሎጂ አሰራርን በማዘመን ጥሩ ውጤት እንዳመጣ ተናግረዋል። ሚኒስትሩ፣ በባጀት ዓመቱ ሩብ ዓመት ለአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ የግብዓት አቅርቦት ከማሳደግ አንጻር በጨርቃጨርቅ፣ በቆዳ፣ በምግብ እና በመጠጥ፣ በኬሚካል እና በኮንስትራክሽን የታቀደው አቅድ መቶ በመቶ ማከናወን መቻሉንም አስረድተዋል ተብሏል፡፡



*የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚንስትሩ የተከበሩ መላኩ አለበል ሪፖርታቸውን ባቀረቡበት ወቅት፤*

ኅዳር 8 2018 ዓ.ም.፣ ተቋማዊ ሪፖርቱን በምክር ቤቱ ለሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የማቅረብ ተራው፣ **የኢኖቬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር** እንደነበር መረጃው ያሳያል። ሚኒስቴሩ ለሌሎች ዘርፎች አጋዥ የሆነ ተቋም መሆኑን የገለፁት የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ፣ ከሌሎች ተቋማት ጋር በቅንጅት መሥራት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መቅረፅ እንደሚገባ አብራርተዋል። የኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ዋናው ዓላማ፣ አዳዲስ ግኝቶችን እና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀም ምርት እና ምርታማነትን ማሳደግ እንደሆነ መናገራቸው የተጠቀሰው ደግሞ፣ የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ ዶ.ር. ቤተልሄም ላቀው ነበሩ ተብሏል።



*የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ እና ምክትል ሰብሳቢዋ የተከበሩ ዶ.ር. ቤቴልሔም ላቀው በሪፖርቱ ወቅት፤*

በሩብ ዓመቱ፣ የውጭ ቱሪስቶች ፍሰት መጠን 250,000 ለማድረስ ታቅዶ 376,615 ቱሪስቶች አገሪቷን እንደጎበኙ የተነገረበት ደግሞ፣ ሌላይኛው የአንደራሴዎቹ የተቋማት ቁጥጥር አንዱ የወሩ ክንውን ነበር። ሪፖርቱን ያቀረበው **የቱሪዝም ሚኒስቴር** ሲሆን፣ ሪፖርቱን ያደመጠው ደግሞ በምክር ቤት የንግድ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መሆኑ ተዘግቧል።



*የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትሯ ሰላማዊት ካሳ ሪፖርታቸውን ባቀረቡበት ወቅት፤*

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ አይሻ ያህያ፣ አገራችን ያላትን የቱሪዝም ፀጋዎች በመጠቀም ባህላዊ እና ተፈጥሯዊ የቱሪዝም ሀብቶቿን በተገቢው መንገድ ለይቶ በማልማት እና በማስተዋወቅ መዳረሻዎችን ማስፋት እንደሚያስፈልግ ገልፀዋል ተብሏል። ሰብሳቢዋ፣ ሉሲ እና ሰላምን በመጠቀም የኢትዮጵያን ምድረ ቀደምትነት በስመ ጥር የአውሮፓ ሚዲያዎች የማስተዋወቅ ሥራ መሠራቱንም በጥንካሬ አክለው ጠቅሰዋል። ሚኒስትሯ ሰላማዊት ካሳ፣ ባለፉት ሦሥት ወራት ከቱሪዝም ዘርፉ 0.938 ቢሊዮን ዶላር ለማድረስ ታቅዶ፣ 1.4 ቢሊዮን ዶላር እንደተገኘ እና አፈጻጸሙ መቶ ከመቶ በላይ መሆኑ በሪፖርታቸው ጠቅሰዋል፡፡ ሚኒስትሯ፣ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት የአገር ውስጥ ጎብኝዎችን መጠን፣ 15 ሚሊዮን ለማድረስ ታቅዶ 23.5 ሚሊዮን ጎብኝዎች የተንቀሳቀሱ መሆኑንም ጨምረው አመላክተዋል ተብሏል፡፡ በገቢ ደረጃም፣ ከአገር ውስጥ ቱሪዝም 26.06 ቢሊዮን ብር ለማድረስ ታቅዶ፣ 32 ቢሊዮን ብር ገቢ መገኘቱን ጠቅሰዋል፡፡

የኅዳር የመጀመሪያ ሳምንት መገባደጃ ላይ ወደ እንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሦሥት ወራት ሪፖርታቸውን ለማቅረብ የሄዱት፣ **የኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት** ዋና ዳይሬክተሯ ወ/ሮ ሰላማዊት ዳዊት ሲሆኑ፤ እርሳቸውም፣ ተቋማቸው በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ አምስት መቶ ዐሥራ አምስት ሺ ፓስፖርት ለዜጎች ማቅረቡን ገልጸዋል ተብሏል። ከዚህ ባለፈም፣ ዐሥራ አንድ ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ ከዐሥር ቢሊዮን ብር በላይ ማሰባሰብ መቻሉንም ዳይሬክተሯ ጠቅሰዋል። በሩብ ዓመቱም፣ ስምንት መቶ ስልሳ ሀሰተኛ ሰነድ ይዘው ፓስፖርት ለመውሰድ የሞከሩ የውጭ ዜጎች እና ኢትዮጵያውያን በቁጥጥር ስር አውሎ በሕግ ተጠያቂ እንዲሆን መቻሉንም ዳይሬክተሯ በሪፖርታቸው ጠቁመዋል ተብሏል።



*የኢሚግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተሯ ወ/ሮ ሰላማዊት ዳዊት ሪፖርታቸውን ሲያቀርቡ፤*

ኅዳር 8 2018 ዓ.ም.፣ የሦሥት ወራት የሥራ አፈጻጸሙን ለምክር ቤቱ የኢንዱስትሪ እና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ያቀረበው፣ አንዱ የፌደራሉ ተቋም **የማዕድን ሚኒስቴር** ሲሆን፤ ሚኒስትሩ ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ፣ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸው በተጠቀሱት ወራት በማዕድን ዘርፉ እየተሰሩ ያሉ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን እና የተከናወኑ አበይት ሥራዎችን እንዲኹም የተገኙ ሌሎች ውጤቶችን ለቋሚ ኮሚቴው አቅርበዋል፡፡ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. አማረች በካሎ፣ የማዕድን ልማቱ ተስፋ ሰጪ መሆኑን ገልፀው፣ በመንግስት በኩል የተጀመሩ ፕሮጀክቶች መጠናቀቃቸው በዘርፉ ተጨማሪ አቅም መፍጠር አስችለዋል ብለዋል ተብሏል። ሚኒስትሩ ኢንጅነር ሀብታሙ በበኩላቸው፣ ከዚህ በፊት በቋሚ ኮሚቴው የተነሱ ጥያቄዎችን በሩብ ዓመቱ ለመመለስ ሰርተናል ሲሉ ለቋሚ ኮሚቴው አባላት ነግረዋቸዋል ተብሏል።



*የማዕድን ሚኒስቴር ሚኒስትሩ ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ ሪፖርታቸውን ሲያቀርቡ፤*

**የኢንቨስትመንት ኮሚሽንም፣** እንደሌሎቹ የተጠቀሱት ተቋማት ኹሉ፣ የባጀት ዓመቱን ሩብ ዓመት ሥራ አፈጻጸም፣ ለምክር ቤቱ የንግድ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ማቅረቡን ምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ አይሻ ያህያ፣ ዋናው የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰት ዓላማ የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ እና የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት እንደሆነ በመጥቀስ፣ ኮሚሽኑ በተሰጠው ኃላፊነት ልክ አቅዶ መሥራት እንደሚገባው አመላክተዋል ተብሏል። ሰብሳቢዋ አክለውም፣ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች 67 በመቶ ድርሻ መያዛቸውን በጥንካሬ ያነሱት ሰብሳቢዋ፣ የውጭም ይሁን የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን ማበረታታት ያስፈልጋል ብለዋል። የውጭ መዋዕለ ንዋይ ፍሰቱ ከአምናው የ8 በመቶ ብልጫ እንዳለው የገለፁት ደግሞ፣ የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ዶ.ር. ዘለቀ ተመስገን ሲሆኑ፤ እርሳቸውም፣ ይኽ እንደአገር የተደረገው የዐብይ ኢኮኖሚው ማሻሻያ እና ኮሚሽኑ ከዲፕሎማቶች ጋር በመቀናጀት ፍላጎትን ዓላማ ያደረገ የማስታወቂያ ሥራ በመሠራቱ የመጣ ውጤት እንደሆነ ገልፀዋል ተብሏል።



*በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የንግድ እና ቱሪዝም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢዋ ወ/ሮ አይሻ ያህያ፤*

ሌላይኛው ተረኛ የወሩ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት አቅራቢ፣ **የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን** እንደነበር የሚጠቅሰው የምክር ቤቱ መረጃ፣ ሪፖርቱንም በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ቋሚ ኮሚቴ ገምግሞታል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ዶ.ር. ነገሪ ሌንጮ፣ የመንግስት አገልግሎቶችን ፈጣን፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ እንዲሆኑ የመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎት ማስፋፋት ላይ የተሰሩ ሥራዎች ትልቅ እምርታ ያስመዘገቡ መሆኑን ገልፀዋል ተብሏል። ሰብሳቢው አክለውም፣ የመንግሥት ሠራተኞችን የኑሮ ኹኔታ ለማሻሻል በአገር ደረጃ የተደረገው የመንግስት የደመወዝ ጭማሪ የሚበረታታ መሆኑን መናገራቸው ተዘግቧል። ያም ሆኖ፣ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚታዩ የመረጃ እና የክፍያ መዘግየት ክፍተቶችን ለማረም በመከታተል መፍትሔ ሊሰጥ እንደሚገባም ሰብሳቢው ጨምረው ጠቁመዋል ተብሏል፡፡

የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ዶ.ር. መኩሪያ ኃይሌም፣ የመሶብ አንድ ማዕከል አገልግሎት ዲጅታል ኢትዮጵያን እውን ከማድረግ አንፃር ከኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ፣ ከኢንሳ እና ከአርቴፊሻል ኢንተለጀንሲ ጋር በመሆን በ23 ተቋማት እንዲኹም በ180 አገልግሎቶች እየተሰጠ መሆኑን አብራርተዋል ተብሏል። የሠራተኛ ምዘናን አስመልክቶ ሰራተኛውን ለመቀነስ ሳይሆን ለተቋማት ተልዕኮ ለማዘጋጀት ዓላማ ያለው እና ክፍተትን ማዕከል ያደረገ ስልጠና በመስጠት ሠራተኛን ለማብቃት እንደሆነ አብራርተዋል።



*የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ዶ.ር. መኩሪያ ኃይሌም የተቋማቸውን ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት፤*

ኢትዮጵያ፣ ከቀጠናው ውጪ ያሉ አገራትን ጨምሮ ከ 34 አገራት የመጡ ስደተኞችን ተቀብላ እያስተናገደች እንደምትገኝ የተሰማበት ሪፖርት የተደመጠው ደግሞ፣ **የኢትዮጵያ ስደተኞች እና ከስደት ተመላሾች አገልግሎት** በምክር ቤቱ ለሚገኘው የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ባቀረበው የሦሥት ወራት የእቅድ አፈጻጸም መሆኑ ተዘግቧል። የተቋሙ ኃላፊ ወ/ሮ ጠይባ ሀሰን፣ በኢትዮጵያ ከሚገኙት ስደተኞች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት ደቡብ ሱዳናውያን ሲሆኑ፤ 33 በመቶዎች ከሶማሊያ፣ 17 በመቶዎቹ ደግሞ የኤርትራ ስደተኞች መሆናቸውን በሪፖርታቸው ጠቅሰዋል ተብሏል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፣ ኢትዮጵያ ካሏት ስደተኞች ቁጥር አንፃር በዓለም ላይ ከለጋሾች እና አጋር አገራት ለስደተኞች ሊደረግ የሚገባው ድጋፍ በመቀነሱ ተፅዕኖው ቀላል ባለመሆኑ አማራጭ የድጋፍ ምንጮችን ለመፈለግ ተቋሙ እያደረገ ያለው ጥረት የሚበረታታ መሆኑን አንስተዋል ተብሏል፡፡ የቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ፈትሂ ማህዲ ዶ/ር በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ስደተኞችን በማስተናገድ 2ኛ ደረጃ መያዟን ጠቅሰው፣ የአገሪቱ ዜጎች የመሠረተ ልማት፣ የኢኮኖሚ፣ የፀጥታ እና የተፈጥሮ ሀብቷ ላይ

ጫና እንዳይፈጥር የማኅበራዊ አገልግሎቶቹን በስፋት ተደራሽ ማድረግ ይገባል ማለታቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷቸዋል።



*የውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ኖጎ፤*

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ የውጭ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የገመገመው ሌላው ተቋም ደግሞ፣ **የብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት** መሆኑን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ዲማ ነጎ፣ ከተቋሙ ተልዕኮ አንፃር በርካታ አገራዊ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ገልፀው፤ ተቋሙ አገራዊ እና ሕዝባዊ ተልዕኮውን በሚገባ እንዲወጣ ለማድረግ ቋሚ ኮሚቴው አስፈላጊውን ድጋፍ እና ክትትል እንደሚያደርግ ተናግረዋል ተብሏል፡፡ የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ፈቲሂ ማህዲ በተራቸው፣ ተቋሙ የሚሰራቸው የመረጃ እና ደኅንነት ሥራዎች ሕዝቡን ያሳተፈ እና ደኅንነቱን የሚያረጋግጡ በመሆናቸው ሥራው ማኅበረሰቡን የበለጠ ማዕከል ያደረገ እንዲሆን የተጀመሩ ጥረቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ አስገንዝበዋል ተብሏል።

## 3.2 የተቋማት እና የመስክ ጉብኝቶች

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ ወርኃ ኅዳርን ያጠናቀቀው ሕግ በማውጣት እና የተቋማትን ሪፖርቶች በማድመጥ ብቻም አልነበረም፤ ከዚያ ተሻግሮም ከአዲስ አበባ እስከ ሲዳማ፣ ከአማራ እስከ ጋምቤላ፣ ከኦሮሚያ እስከ ሱማሌ ክልሎች ድረስ ያሉ የፌደራል ተቋማትን በተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎቹ በኩል ሲጎበኝ፤ አርባ ኹለት የሚሆኑ የመስክ ጉብኝቶችንም አድርጓል፤ እንደራሴም ማሳያ ይሆናሉ ያለቻቸውን ጉብኝቶች እንደሚከተለው ጠቅልላ ተመልክታቸዋለች።

### 3.2.1 የተቋማቱ ጉብኝቶች

እንደራሴዎቹ በወርኃ ኅዳር ከጎበኟቸው የፌደራል ተቋማት መካከል ቀዳሚ ማሳያ የሚሆነው፣ የምክር ቤቱ የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ **በገላን፣ ቃሊቲ እና ቂሊንጦ የፌደራሉ ማረሚያ ቤቶች** ውስጥ ያደረገው ጉብኝት ነው። ቋሚ ኮሚቴው፣ በማረሚያ ቤቱ የመስክ ምልከታ ባደረገበት ወቅት የታራሚዎችን መጠለያ፣ መመገቢያ፣ የውኃ እና የምግብ አቅርቦቶችን እና የተለያዩ የሙያ ማሠልጠኛዎችን እንዲሁም የታራሚ ተማሪዎች 2ኛ ደረጃ መማሪያ ክፍሎችን ተዘዋውሮ ተመልክቷል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ እፀገነት መንግስቱ፣ የገላን የጥበቃ ማዕከል የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት የታራሚዎች አያያዝ ሕግ እና ሥርዓትን ያከበረ መሆን እንዳለበት ጠቁመዋል ተብሏል። አያይዘውም ታራሚዎች በቆይታቸው ታርመው እና ታንፀው እንዲወጡ በተለይም ወንድማማችነትን እና እህትማማችነትን ያጎለበተ ተቋም እንዲሆን መሥራት እንዳለባቸው አመላክተዋል። ሰብሳቢዋ አክለውም፣ አካል ጉዳተኛ የሕግ ታራሚዎችን ታሳቢ ያደረገ ምቹ የመመገቢያ እና የማደሪያ ቦታ ማመቻቸት እንደሚገባ፣ እንዲሁም የሥነ-አዕምሮ ታማሚ የሆኑ ታራሚዎችን የሕክምና መረጃን መሰረት በማድረግ ለአእምሮ ህሙማን ማዕከል ማስረከብ እንደሚገባ መናገራቸውን የምክር ቤቱ ሪፖርት ጠቅሷቸዋል።



*የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው በገላን፣ ቃሊቲ እና ቂሊንጦ የፌደራሉ ማረሚያ ቤቶች ጉብኝቱ ወቅት፤*

እንደ ምክር ቤቱ መረጃ ከሆነም፣ ይኸው ቋሚ ኮሚቴ፣ **በፍትሕ ሚኒስቴር የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ** የሥራ እንቅስቃሴን ተመልክቷል፡፡ ሰብሳቢዋ የተከበሩ ወ/ሮ እፀገነት፣ የፍትሕ ሥርዓቱን ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማሳደግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር እና በቅንጅት በመሥራት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እያደረገ ያለው ጥረት ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ጠቁመዋል ተብሏል፡ ፡ የፍትሕ ሚኒስቴር ሚኒስትሯ ወ/ሮ ሃና አርዓያ ሥላሴም፣ የፍትሕ ሥርዓቱን በማሻሻል ለኅብረተሰቡ ተደራሽ ለመሆን ከሚመለከታቸው የሕግ አካላት ጋር በትብብር እና በቅንጅት በመሥራት ውጤታማ ሥራዎችን ማከናወን መቻሉን በዚያ ላገኟቸው የቋሚ ኮሚቴው አባላት አስረድተዋል። ከዚያ ባለፈም፣ የአመራር ቅንጅታዊ አሰራር ሚናው የጎላ በመሆኑ፣ የፍትሕ ተቋማት ተልዕኳቸውን በአግባቡ ለመወጣት ቅንጅታዊ አሰራሮችን በይበልጥ አጠናክረው እንደሚሰሩ ሚኒስትሯ መግለፃቸውን መረጃው ጠቅሷቸዋል።

ሌላይኛው የወሩ ተጎብኚ ማሳያ ተቋም፣ **በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት** ሲሆን፣ ወደዚህ ተቋም የደረሱት ደግሞ፣ በምክር ቤቱ የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እንደነበር መረጃው ያሳያል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ደሳለኝ ወዳጄ፣ የጉብኝቱ አላማ ጽሕፈት ቤቱ የመንግስት የልማት ዕቅዶችን ተግባራዊ ለማድረግ የወጡ ሕግጋት፣ ደንቦች እና መመሪያዎችን መሰረት ያደረጉ፣ ግልጸኝነት እና ተጠያቂነትን በማስፈን ከብልሹ አሰራር በፀዳ መልኩ ተግባራት እየፈጸመ መሆኑን በማየት፣ የሕዝብን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል፡፡ የቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ የፕላን እና ለውጥ ሥራዎች የሥራ ሂደት አስተባባሪ ወ/ሮ አየለች ጡምዶሎም፣ በዚያ ላገኟቸው የቋሚ ኮሚቴ አባላት የጽሕፈት ትኣቸውን የሩብ ዓመት አፈጻጸም ማቅረባቸውም ታውቋል። በሩብ ዓመቱ 13 ቢሊየን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 12.99 ቢሊየን ብር መሰብሰቡን የጠቀሱት አስተባባሪዋ፣ የውርስ መጋዘን ዕቃዎች አወጋገድ መመሪያ የኤርፖርትን ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ ያደረገ ሆኖ ቢሻሻል ሲሉም ለቋሚ ኮሚቴው አባላት ሐሳባቸውን ሰንዝረዋል።



*በምክር ቤቱ የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ጉብኝቱ ወቅት፤*

በኅዳር የመጀመሪያ ሳምንት፣ **ቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሕክምና ኮሌጅ** የደረሱት፣ በምክር ቤቱ የመንግስት ወጪ አሥተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ሲሆኑ፣ የጉብኝቱ አላማም፣ የፌዴራል ዋና ኦዲተር ለኮሌጅ የክዋኔ ኦዲት ግኝቶች ላይ ማሻሻያ እንዲያደርግ በሰጠው ምክረ-ሐሳብ መሰረት የእርምት ማስተካከያ ማድረጉን ለማረጋገጥ እንደነበር ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ያሳያል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ አራሬ ሞሲሳ፣ ኮሌጁ ደረቅ

ቆሻሻን በአግባቡ ለማስወገድ ኢኮስትሪል የተሰኘው ማሽን ተተክሎ ሥራ ሊጀምር ቅድመ ዝግጅቱ መጠናቀቁ በአዎንታዊነት የሚታይ እንደሆነ ገልጸዋል ተብሏል፡፡ በሌላ በኩል በጤና ሚኒስቴር አማካኝነት በቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ ዙሪያ የሕግ ማዕቀፍ ወጥቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣ አሁንም በሆስፒታሎች እንደ ክዋኔ ኦዲት ግኝት የሚታይ ችግር መሆኑን ሰብሳቢዋ ገልጸዋል ተብሏል፡፡




***የመንግስት ወጪ አሥተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ ኮሌጁን ሲጎበኙ፤***

በኅዳር ወር አጋማሽ፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት የተጎበኘው ሌላይኛው፣ **የፌደራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት** ነበር። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ኢሳ ቦሩ፣ የሸሪዓ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአገልግሎት አሰጣጥ፤ ከበጀት እና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም አንፃር እንዲሁም ሠራተኞችን እና ዳኞችን ከማሠልጠን እና ከማብቃት ጋር በተያያዘ ያሉበትን ክፍተቶች ማስተካከል እንዳለበት አስገንዝበዋል ተብሏል፡፡ የቋሚ ኮሚቴው አባላት በበኩላቸው፣ በጀትን ለታለመለት ዓላማ ከማዋል ጋር በተያያዘ ያሉትን አሰራሮች መፈተሽ እና ማስተካከል እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡ በተያያዘ መረጃም፣ ቋሚ ኮሚቴው የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ጋር በተያያዘ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት በሚያስችል መልኩ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከፍተኛ አመራሮች በተገኙበት ግብረ መልስ መስጠቱ ታውቋል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ኢሳ ቦሩም፣ የሸሪዓ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመንግሥት ተቋም ቢሆንም ወቅቱን የሚመጥን የመንግሥት የአሰራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት የማሻሻያ ሥራዎችን መተግበር እንደሚገባ አስገንዝበዋል ተብሏል፡፡



***የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የፌደራል ጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤትን በጎበኙበት ወቅት፤***

ይኸው ቋሚ ኮሚቴ በወሩ የጎበኘው ሌላው ተቋም **የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ** ሲሆን፣ ቋሚ ኮሚቴውም የዩኒቨርሲቲውን የወንጀል ምርመራ ቤተ ሙከራዎችን፣ የፎረንሲክ እና በዘርፉ ወንጀልን ለመከላከል የሚያስችሉ የተለያዩ የምርመራ የናሙና ውጤቶችን መመልከቱን መረጃው ያሳያል። ሰብሳቢው የተከበሩ ኢሳም፣ ዩኒቨርሲቲው በወንጀል ምርመራ በፎረንሲክ የታገዘ እና ዘመኑን የዋጀ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የሕዝቡን ሰላም እና ደኅንነት ለመጠበቅ እና የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ እየሰራቸው ያሉ ሥራዎች አበረታች መሆናቸውን ገልጸዋል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው አባላትም፣ ተቋሙ የዲጂታል ሥርዓትን እንደአገር የተያዘውን ራዕይ እውን ለማድረግ እያደረገ ያለው ጥረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማስገንዘባቸው ተዘግቧል።

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተጎበኘው **የኢትዮጵያ መድን ድርጅት፣** የወሩ አንዱ ተጎብኚ ማሳያ ተቋም

ነበር። እንደ መረጃው ከሆነም፣ ቋሚ ኮሚቴው በድርጅቱ ድንገተኛ ምልከታ ያደረገ ሲሆን፣ በድርጅቱ እየተከናወኑ ያሉ የማሻሻያ ሥራዎችን ተዘዋውሮ ተመልክቷል፡፡ በዚህም፣ ድርጅቱ የማሻሻያ ሥራዎችን መጀመሩን፣ የሩብ ዓመት አፈጻጸሙ ከአምናው ተመሳሳይ ጊዜ ሲነጻጸር የተሻለ መሆኑ እና ድርጅቱን አቅም ባለው የሰው ኃይል ለማሟላት የተሰራው ሥራ ውጤታማ መሆኑን የተናገሩት ደግሞ፣ የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ኢንጂነር ስለሽ ኮሬ መሆናቸው ተጠቅሷል። ከዚህ በተጨማሪም፣ ለሠራተኞች ምቹ የሥራ ከባቢ ከመፍጠር አኳያ ውስንነት መኖሩን እና የድርጅቱን ወጪዎች ተገቢ በሆነ እና ውጤታማ ሥራዎች ላይ ማዋል እንደሚገባም ምክትል ሰብሳቢው አስገንዝበዋል ተብሏል፡፡



*የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የኢትዮጵያ መድን ድርጅትን ሲጎበኙ፤*

በወርኃ ኅዳር፣ በእንደራሴዎቹ ከተጎበኙ የፌደራል ተቋማት መካከል ማሳያ ሊሆን የሚችለው ሌላኛው ተቋም፣ **የኢትዮጵያ ምግብ እና መድኃኒት ባለስልጣን** ሲሆን፤ ወደ ተቋሙ የሄዱትም፣ በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ነበሩ ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ታደለ ቡራቃም፣ ተቋሙ የጥራት ደረጃው ሌሎች አገራት የደረሱበትን ያሟላ እንዲሆን፣ የሌሎችን ተሞክሮ መውሰድ እንደሚያስፈልግ አንስተው፣ ተቋሙ መፍጠን የሚገባውን ያህል እንዳይሄድ ያስቸገሩ ጉዳዮችን ማየት እንደሚገባው አሳስበዋል ተብሏል። ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ለነገ የማይባል እንደሆነ ጨምረው ያነሱት ሰብሳቢው፣ ባለሥልጣኑ ጥሩ የሚሰሩትን የሚያበረታታ፣ ያልሰሩትን ደግሞ ተጠያቂ የሚያደርግበትን ሥርዓት መዘርጋት አለበት ብለዋል ተብሏል። የኢትዮጵያ ምግብ እና መድኃኒት ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ነጋሽ ስሜ በበኩላቸው፣ ተቋሙ ዓመታዊ እቅዱን ለኹሉም የሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች የጋራ አድርጎ ስለመጀመሩ አንስተው፣ የማኅበረሰቡን ጤና ለመጠበቅ በምግብ፣ በመድኃኒት፣ በትንባሆ እና በሕክምና መሳሪያ ጥራት እና ውጤታማነትን ለማስጠበቅ እየሰሩ መሆኑን መግለጻቸው ተዘግቧል።




*የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የኢትዮጵያ የኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩትን በጎበኙበት ወቅት፤*

ወደሌላኛው የፌደራል ተቋም ወደ ሆነው **የኢትዮጵያ የኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት** የደረሱት እነኹ የቋሚ ኮሚቴው አባላት፣ የማርበርግ በሽታን ከመከላከል እና ከመቆጣጠር አንጻር በተጨባጭ ምን እየተሰራ እንደሆነ ለመመልከት መጓዛቸውን ጠቅሰዋል። ምክትል ሰብሳቢው የተከበሩ ዶ.ር. ታደለ ቡራቃ፣ በሽታው ድንበር ተሻጋሪ ከመሆኑ አንጻር፣ በድንበር አካባቢ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች ያሉበት ሁኔታ እንዲሁም ድንበር አካባቢ የቅኝት ሥራ እና የለይቶ ማቆያ ቦታ ዝግጅት ሥራ

ምን እንደሚመስል ለተቋሙ ኅላፊዎች አንስተውላቸዋል ተብሏል። የኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ዶ.ር. መሳይ ኃይሉ በበኩላቸው፣ ኢንስቲትዩቱ በተሰጠው ተልዕኮ መሠረት የቅኝት ሥራዎችን፣ የቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ድንበር ተሻጋሪ በሽታዎችን የመከላከል እና የመቆጣጠር ሥራ እንደሚሰራ ጠቅሰዋል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው አባላት በበኩላቸው፣ በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ መሥራት እና በሽታውን ለመከላከል ከመንግስት እና ከግል የጤና ተቋማት ጋር በቅንጅት ሊሠራ ይገባል ማለታቸው ተጠቅሷል።

በወሩ ከተጎበኙት ተቋማት መካከል ሌላይኛው **ብሔራዊ ሎተሪ አሥተዳደር** ሲሆን፤ ጉብኝቱንም የከወኑት በእንደራዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መሆኑ ተጠቅሷል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መና፣ የተቋሙን የ2018 ባጀት የ1ኛ ሩብ ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ ሪፖርት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርትን በመገምገም፣ ቋሚ ኮሚቴው ሙያዊ እና አሥተዳደራዊ ድጋፍ እንደሚያደርግ ጠቁመዋል ተብሏል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ኢንጂነር ስለሽ ኮሬ በበኩላቸው፣ ተቋሙ የጀመራቸውን ሥራዎች ከግብ ለማድረስ በእቅድ አካቶ ተፈፃሚነታቸውን ለማረጋገጥ አገራዊ እና ተቋማዊ ለውጥን ታሳቢ ማድረግ እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡ የቋሚ ኮሚቴው አባላት በበኩላቸው፣ በቴክኖሎጂ የተጋዘ የቁጥጥር እና የክትትል ሥራዎችን በማጠናከር ሕገ-ወጥ አሰራሮችን በመከላከል መንግስት አስፈላጊውን ግብር እንዲያገኝ ለማስቻል አሰራሮችን በጥብቅ ዲስፕሊን ማስፈጸም እንደሚገባ ማስገንዘባቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።



*የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ ብሔራዊ ሎተሪ አሥተዳደርን ሲጎበኙ፤*

በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ኅዳር ወር የመጎብኘት ዕጣ የደረሰው ሌላይኛው ተቋም፣ **የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት** ሲሆን፤ ጉብኙቱንም የከወነው በምክር ቤቱ የኢንዱስትሪ እና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መሆኑን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷል። የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ፍቃዱ መንግስቱ፣ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩቱ የማዕድን ዘርፉን ለማነቃቃት እና ለማሸጋገር የማይተካ ሚና እያከናወነ መሆኑን መናገራቸውን ይኸው ዘገባ ጠቅሷል። ሌሎቹ የቋሚ ኮሚቴው አባላት በበኩላቸው፣ ኢንስቲትዩቱ እያስገነባ ያለው ላብራቶሪ እና ሌሎች ጀምር ሥራዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት መጠናቀቅ እንዳለባቸው አሳስበዋል ተብሏል።



*የኢንዱስትሪ እና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩትን ሲጎበኙ፤*

### 3.2.2 የመስክ ጉብኝቶች

በዚኽ ሽፋን በሰጠነው ኅዳር ወር፣ የእንደራሴዎቹ ካደረጓቸው የመስክ ጉብኝቶች መካከል በቀን ምጣኔ ሊጠቀስ የሚችለው፣ **በሲዳማ ብሔራዊ ክልል** በምክር ቤቱ የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተካሄደው ጉብኝት ነው። ቋሚ ኮሚቴ በምልከታው፣ በሀዋሳ ከተማ አሥተዳደር የጤና መምሪያ ስር በሚገኙ የሐዋሳ ሚሊኒየም ጤና ጣቢያ እና ሞቴተ ፉራ የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታልን ጠቅላላ የሥራ እንቅስቃሴ ተመልክቷል ተብሏል።

የአሠራር ሥርዓቱን ሙሉ በሙሉ ከወረቀት ነጻ በማድረግ ለኅብረተሰቡ ጥራት ያለው የሕክምና አገልግሎት በመስጠት የሚገኘው ሆስፒታሉ፣ የራጅ ማሽን እና የጨቅላ ሕጻናት መሞቂያ ማሽን እጥረት እንዳለበት የቋሚ ኮሚቴው አባል እና አስተባባሪ የተከበሩ ዶ.ር ማኅተመ ኃይሌ መግለጻቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። የሆስፒታሉ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሄኖክ ገልፈቶ በበኩላቸው፣ ሆስፒታሉ አገልግሎቱን ለኅብረተሰቡ በተሻለ ኹኔታ ተደራሽ ለማድረግ የቦታ ጥበት ችግር ስላለበት የማስፋፊያ ግንባታ ለመሥራት መቸገሩን ገልጸዋል። በሌላ በኩል በሚሊኒየም ጤና ጣቢያ ለሚሰጠው የነጻ ሕክምና አገልግሎት የመተኪያ ክፍያ መዘግየት በጤና ተቋሙ ላይ ችግር እየፈጠረ እንደሆነ የጤና ጣቢያው ኃላፊ አቶ ኤፍሬም ተሰማ ተናግረዋል ተብሏል።

ይኸው ቋሚ ኮሚቴ፣ በክልሉ የሚገኘውን የሲዳማ ክልል ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ላይ የመስክ ጉብኝት አካሂዷል። የቡድኑ መሪ የተከበሩ ዶ.ር. ማኅተመ ኃይሌ፣ ኢንስቲትዩቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተቋቁሞ ጥራቱን የጠበቀ የሪፈራንስ የላብራቶሪ አገልግሎት፣ ለአገር ሞዴል የሚሆኑ የተቢ ሕሙማን የምርመራ ውጤት ለጤና ድርጅቶች በወቅቱ የሚገለፅበት ሥርዓት መዘርጋት እና የወረርሽኝ ጭምጭምታ መረጃዎች መመዝገቢያ ሶፍትዌር ማጎልበትን በተመለከተ የተሰሩ ተግባራትን አድንቀዋል ተብሏል። የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ዶ.ር. ዳመን ደባልቄ፣ የክልሉ መንግስት በአሁኑ ወቅት በአጎራባች ክልል የተከሰተውን የማርበርግ ቫይረስን ለመከላከል እንዲረዳ በክልሉ እና በየደረጃው የሚገኙ የአሥተዳደር እርከኖች ወረርሽኙን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚያስችል ኹለት ሚሊዮን ብር በመመደብ፣ ከመንግስት እና ከግል ጤና ተቋማት የጤና ባለሙያዎች የሚገኙበት ግብረ ኃይል በማቋቋም ሥልጠና በመስጠት ስለበሽታው ግንዛቤ መፍጠር መቻሉን ገልጸዋል ተብሏል።



*የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሲዳማ ጉብኝቱ ወቅት፤*

ኅዳር አጋማሽ ላይ በእንደራሴዎቹ የተጎበኘው ሀዋሳ ሕክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አጠቃላይ ልዩ ሆስፒታልም አንዱ ተጠቃሽ የወሩ ተጎብኚ ተቋም ነበር። ሆስፒታሉን የጎበኘው በምክር ቤቱ የመንግሥት ወጪ አሥተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባል እና የቡድኑ መሪ የተከበሩ ደረጀ ደበላም፣ ኮሌጁ የደረቅ እና ፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ አካባቢን እንዳይበክል ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበዋል ተብሏል፡፡ የተከበሩ ደረጀ አክለውም፣ ከሆስፒታሉ የሚወጣው ቆሻሻ አካባቢን እንዳይበክል የቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድን ማዘመን እንደሚገባ መናገራቸው ተዘግቧል።



*የመንግሥት ወጪ አሠተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የሀዋሳ ሕክምና እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅን ሲጎበኝ፤*

የቋሚ ኮሚቴው አባላት በበኩላቸው፣ ከደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያው የሚወጣው ጭስ የአካባቢውን አየር ሊበክል ስለሚችል ጥንቃቄ ሊድረግ ይገባል ማለታቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች በወርኃ ኅዳር ካደረጓቸው የመስክ ጉብኝቶች ሊጠቀስ የሚችለው፣ ወደ **አማራ ክልል** መቀመጫ ያደረጉት ጉብኝት ነው። የባሕር ዳር ስታዲየምን የጎበኙት በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት ሲሆኑ፣ የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. ታደለ ቡራቃም፣ አገራችን በስፖርት ዘርፍ አኩሪ ታሪክ ያላት ብትሆንም፣ በዘርፉ ያላትን ታሪክ የሚመጥኑ ደረጃቸውን የጠበቁ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ባለመኖራቸው የተነሳ ዓለም ዓቀፍ ውድድሮችን ለማስተናገድ አለመቻሉን ገልጸዋል ተብሏል፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ወ/ሮ ሸዊት ሻንካ በበኩላቸው፣ የባሕር ዳር ስታዲየም ግንባታው ከተጠናቀቀ ዓመታትን ቢያስቆጥርም፣ የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደሬሽን ደረጃን ያሟላ ባለመሆኑ ዓለም ዓቀፍ ውድድሮችን እንዳያከናውን ታግዶ እንደነበር ጠቅሰዋል። አሁን ግን፣ ስታዲየሙ ሁሉንም አይነት አሕጉራዊ እና ዓለም ዓቀፋዊ ውድድሮችን ማስተናገድ እንደሚችል ለቋሚ ኮሚቴው አባላት ነግረዋቸዋል።



*የጤና፣ ማኅበራዊ ልማት፣ ባህል እና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴው፣ በባሕርዳር ስታዲየም ጉብኝት ወቅት፤*

ኅዳር አጋማሽ ላይ ወደ ምሥራቃዊቷ **ሱማሌ ክልል** የደረሱት፣ በምክር ቤቱ የፕላን፣ ባጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ ከክልሉ ርዕሰ-መሥተዳድር ጋር ከመወያየታቸው ባለፈ የመስክ ጉብኝትም አድርገዋል። የቋሚ ኮሚቴው አባል እና የቡድን መሪ የተከበሩ ወ/ሮ አስቴር ከፍታው፣ የድጎማ እና የዘላቂ ልማት ግቦች ማስፈጸሚያ ባጀቶች በአግባቡ በሥራ ላይ ለመዋላቸው ቁጥጥር እና ክትትል እንደሚደረግባቸው አንስተዋል ተብሏል። የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊው አቶ ደይብ አህመድ በበኩላቸው፣ ለተቋማት በተደለደለው ባጀት መሰረት በትምህርት፣ በጤና፣ በመሠረተ- ልማት እና በተለያዩ ዘርፎች ጠንካራ አፈፃፀም የተመዘገበ መሆኑን አብራርተዋል። ቋሚ ኮሚቴውም በሰጠው ግብረ መልስ፣ ቢሮው የመንግስት ፋይናንስን ከማሥተዳደር አኳያ እያከናወነ ያለውን የመደበኛ ባጀት አጠቃቀም እና አፈጻጸም፣ ክልሉ በ2018 ዓ.ም. ከፌዴራል መንግስት የተመደበለትን ከመጠቀም እና ከማሥተዳደር አንፃር የ1ኛ ሩብ ዓመት አፈጻጸሙ የሚበረታታ ነው ብሏል ተብሏል።

ከክልሉ ርዕሰ-መሥተዳድር ክቡር ሙስጠፌ መሐመድ ጋርም መወያየቱ የተሰማው ቋሚ ኮሚቴው፣ የመሠረተ ልማት ፍላጎቶችን ለማሟላት ክልሉ እያደረገ ያለው

ጥረት የሚበረታታ መሆኑን በመስክ ምልከታ ማረጋገጡን ጠቁሞ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረው "አንድ ዕቅድ አንድ ሪፖርት" በጅግጅጋም ተግባራዊ መደረጉን መጥቀሱን የምክር ቤቱ መረጃ ያሳያል። ርዕሰ-መሥተዳድሩ ሙስጠፌ መሐመድ በበኩላቸው፣ ቋሚ ኮሚቴው በየጊዜው ለሚያደርገው ክትትል እና ቁጥጥር ምስጋና አቅርበው፣ የተሰጠውን ግብረ-መልስ በመቀበል በጥንካሬ የተነሱት እንዲቀጥሉ፣ መስተካከል ያለባቸውም እንዲስተካከሉ ለማድረግ እንደሚሰራም ጠቁመዋል ተብሏል።




***የፕላን፣ ባጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ ከክልሉ ርዕሰ-መሥተዳድር ክቡር ሙስጠፌ መሐመድ ጋር ሲወያዩ፤***

እነህን መሰል የመስክ ጉብኞቶችን ያከናወኑት እንደራሴዎቹ፣ በምክር ቤቱ የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በኩልም ወደ ምዕራባዊዋ **ጋምቤላ ክልል**ም ደርሰው እንደነበር ተዘግቧል። ጋምቤላ የደረሱት የቋሚ ኮሚቴው ቡድን አሥተባባሪ የተከበሩ ወ/ሮ ከድጃ ያሲን፣ የዳኝነት ሥራን በሁሉም አካባቢ ተደራሽ ከማድረግ፣ ውጤታማ እና ፍትሐዊ የወንጀል ሥርዓት ከመዘርጋት እንዲሁም ፍትሕ ቢሮ በቴክኖሎጂ በመታገዝ ቀልጣፋ አገልግሎት ከመስጠት አኳያ የተሰሩ ሥራዎችን በመስክ ምልከታቸው እንዳዩ ተናግረዋል ተብሏል። ወደዚያው ክልል የሄዱት ሌሎኞቹ የኢንዱስትሪ እና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላትም፣ የኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም፣ የውጭ ምንዛሪ ገቢን፣ የማኅበረሰብ ተጠቃሚነትን፣ የሥራ እድል ፈጠራን እና የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰትን መሳብን አስመልክቶ ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን በመገምገም ግብረ መልስ የሚሰጥ መሆኑን የቡድኑ መሪ የተከበሩ ፍቃዱ ሞሲሳ መናገራቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።



***የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ በጋምቤላ ክልል የመስክ ጉብኝት ወቅት፤***

ኅዳር መገባደጃ ላይ ወደ **ወላይታ ሶዶ** የተጓዙት፣ በምክር ቤቱ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ ከዞኑ የሥራ ኃላፊዎች ጋር የገሱባ-ጋርቤ-ቃንቆ 15 ኪሎ ሜትር አዲስ መንገድ ግንባታ ያለበትን ደረጃ ለማወቅ የመስክ ምልከታ አድርገዋል። የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መና፣ መንግሥት የሕዝቡን የልማት ጥያቄ ለመፍታት ዝግጁ መሆኑን ተናግረዋል ተብሏል። ከዚኽ ባለፈም ሰብሳቢው፣ ሕዝብ የልማት ጠያቂ እና የመንግሥት እጅ ጠባቂ ብቻ ሳይሆን ራሱ የሚሠራ መሆን አለበት ማለታቸውን የምክር ቤቱ ዘገባ ጠቅሷቸዋል።

## 4. የውክልና ሥራ

የኢትዮጵያ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በእረፍት እና የሥራ ጊዜ ማሻሻያ ዐዋጅ ቁጥር 263/1994 ዓ.ም. መሰረት፣ የእንደራሴዎቹ የእረፍት ጊዜ በየዓመቱ ከየካቲት 1 እስከ 30 እና ከሐምሌ 1 እስከ መስከረም ወር የመጨረሻ ሳምንት ሰኞ ዋዜማ ድረስ መሆኑ ተደንግጓል። ያም ሆኖ፣ የምክር ቤቱ ኹለት እንደራሴዎች በዚኽ ሽፋን በሰጠነው ወርኃ ኅዳር፣ ሕገ-መንግሥታዊ ኀላፊነታቸው የሆነውን የውክልና ሥራም ተግብረዋል።

ኅዳር የመጀመሪያ ሳምንት ላይ ወደ ሠቃ ጨቆርሣ የሄዱት የተከበሩ ወ/ሮ ለጢፋ አባተማም፣ ለረጅም ጊዜ የቆየውን ውስብስብ የገጠር መንገድ ጥገና ችግር ለመፍታት የወረዳውን ተወላጆች እና ወዳጆችን በማስተባበር በ24 ሚሊየን ብር ግሬደር ተገዝቶ እንዲቀርብ አድርገዋል ተብሏል። ባለፉት ዓመታት፣ እንደራሴዋ ከመረጣቸው ሕዝብ ጋር በመከሩበት ወቅት ሕዝቡ በተደጋጋሚ ሲያነሳቸው ከቆዩ ጉዳዮች ውስጥ የገጠር መንገድ ውስብስብ ችግር አንዱ መሆኑም ተገልጿል ተብሏል።



*የተከበሩ ወ/ሮ ለጢፋ አባተማም፣ በውክልና ሥራቸው ወቅት፤*

ለመሰል ሕገ-መንግሥታዊ ግብር ደደር የተገኙት የተከበሩ ዶ.ር. ኤልያስ አህመድ፣ የተለያዩ አካላትን በማስተባበር፣ በወረዳው እና በከተማ አሥተዳደሩ እንዲሁም በአካባቢው ማኅረሰብ ተሳትፎ በደደር አጠቃላይ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፤ በኪዮ መለስተኛ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንዲሁም በሶቃ ኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደግሞ የዲጂታል ቤተ-መጻሕፍት እንዲቋቋም ማድረጋቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ጠቁሟል።



*የተከበሩ ዶ.ር. ኤልያስ አህመድ፣ በውክልና ሥራቸው ላይ፤*

## 5. የፓርላማ ዲፕሎማሲ

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት፣ በወርኃ ኅዳር የከወነው ፓርላመንታዊ ዲፕሎማሲ አንድ ብቻ እንደነበር የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቁማል።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ **ከአዘርባጃን ፕሬዝደንት ልዩ መልዕክተኛ** ጋር ያደረጉት ውይይት እንደነበር ተጠቅሷል። ኢትዮጵያ የባንኪንግ፣ የፋይናንስ እና የንግድ ክፍለ-ኢኮኖሚዋን በማዘመን ላይ እንደምትገኝ ያነሱት አፈ-ጉባኤው፣ በአገራቱ መካከል ያለው የባህል፣ የሕዝብ-ለሕዝብ እና የቱሪዝም ግንኙነትን ለማሳደግ በትኩረት እንደሚሰራ አመላክተዋል ተብሏል። የአዘርባጃን ፕሬዝደንት ልዩ መልዕክተኛው የተከበሩ ኤልቺን አምራባዮቭ በበኩላቸው፣ አዘርባጃን ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ዘርፈ ብዙ ግንኙነት ለማሳደግ ፍላጎት እንዳላት ገልጸዋል ተብሏል። አዘርባጃን በኢትዮጵያ በንግድ፣ ኢንዱስትሪ እና ግብርና ዘርፎች ለመሰማራት ፍላጎት አላት ያሉት ልዩ መልዕክተኛው፣ አገራቸው ለኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ነፃ የትምህርት ዕድል በመስጠት ላይ እንደምትገኝ መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል።



*አፈ-ጉባኤ የተከበሩ ታገሰ ጫፎ፣ ከአዘርባጃን ፕሬዝደንት ልዩ መልዕክተኛ ጋር ሲወያዩ፤*

## 6. እንደራሴዎቹ ስለ'ራሳቸው

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ ወርኃ ኅዳርን ያገባደደው ከላይ አጠር አድርገን የዳሰስናቸውን ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነቶች በመከወን ብቻም ሳይሆን፣ ለአባላቱ ይሆኑኛል ያላቸውን ሥልጠናዎች በመስጠት እና የ2018 ዓ.ም. የሩብ ዓመት አፈጻጸሙን በመገምገምም ነበር።

የኢፌድሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ለጽሕፈት ቤቱ አመራሮች እና ሠራተኞች **ሥነ-ምግባራዊ አመራርነትን ማጎልበት** በሚል ርዕስ ሥልጠና ሰጥቼያለሁ ብሏል። በወቅቱ፣ በምክር ቤት ጽሕፈት ቤቱ የሙያዊ ድጋፍ ዘርፍ ምክትል ዋና ጸሐፊው ዶ.ር. ንጉሴ መሸሻ፣ መልካም ሥነ-ምግባር ፈጠራን በማጎልበት እና በአመራር እና በሠራተኛው መካከል መተማመንን በመፍጠር የተቋምን የመፈጸም አቅም ለማሳደግ ያግዛል ብለዋል ተብሏል። ቡድናዊ መንፈስን በመገንባት እና ከአድልዎ የፀዳ አገልግሎት በመስጠት ለአንድ ዓላማ በቁርጠኝነት መሥራት ከሠራተኛው የሚጠበቅ መሆኑንም ምክትል ዋና ጸሐፊው አክለው ጠቅሰዋል። ሥልጠናውን የሰጡት የሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ መምህሩ ዶ.ር. ተሰፋዬ ሂርጳሳ በበኩላቸው፣ ሥነ- ምግባር በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ በጋራ የሚዳብር እና የሚተገበር መሆኑን አመላክተዋል። ሙስና ከመንግስት ወይም ከሕዝብ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ገፊ ምክንያት ሲኖር፣ መልካም አጋጣሚዎች ሲፈጠሩ ወይም በምክንያት የሚፈጸም የወንጀል አይነት እንደሆነ የጠቀሱት አሠልጣኙ፣ ትውልዱ ላይ በመሥራት ችግሩን መቀነስ እንደሚቻል መናገራቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ይጠቅሳል።



*እንደራሴዎቹ በሥልጠና ላይ ሳሉ፤*

የስፖይ እና ቢፊዳ እና ሃይሮሴፋለስ በሽታን መከላከል የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ትኩረት ይፈልጋል ሲሉ፣ የምክር ቤቱ ምክትል አፈ-ጉባኤ ወ/ሮ ሎሚ በዶ የተናገሩበት መድረክ ደግሞ ኹለተኛው የወሩ የእንደራሴዎቹ የሥልጠና መድረክ ነበር። በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ለ14ኛ፣ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ7ኛ ጊዜ የተከበረውን **የስፖይና ቢፊዳ እና ሃይሮሴፋለስ ቀን** አስመልክቶ ሥልጠናው መሰጠቱን መረጃው ይጠቁማል። ሆፕ የተሰኘ ግብረ ሰናይ ድርጅት ከምክር ቤቱ ጋር በመተባበር ለእንደራሴዎቹ ባዘጋጀው የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ላይ ተገኝተው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የተከበሩ ወ/ሮ ሎሚ፣ በአገራችን ሕፃናትን ብቻ ሳይሆን በአገሪቱም እድገት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳደረ በመሆኑ፣ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው በመሥራት ውጤት ማምጣት ይጠበቅባቸዋል ብለዋል ተብሏል። አክለውም፣ የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴዎችም የጋራ እቅድ አውጥተው በመሥራት የወጡ ሕግጋት ተግባራዊ መደረጋቸውን ማረጋገጥ እና ተጠያቂነትን ማስፈን ይገባቸዋል ሲሉም አስገንዝበዋል፡፡ የድርጅቱ መስራች እና ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ ቤዛ በሻ በበኩላቸው፣ ይኽንን በሕጻናት ላይ የሚከሰት የነርቭ ዘንግ እና የጭንቅላት በሽታን ለመከላከል በባጀትም በሕግም መደገፍ እንደሚገባ ጠቁመው፣ በምክር ቤቱ በኩል ለጉዳዩ የተሰጠው ትኩረት

የበለጠ ለመሥራት መነሳሳት የፈጠረላቸው መሆኑን መጥቀሳቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

የወሩ ሦሥተኛው የሥልጠና መድረክ የተዘጋጀው ለሴት እንደራሴዎቹ ሲሆን፤ የሥልጠናው ርዕሰ-ጉዳይም፣ **በስትራቴጂካዊ ዕቅድ ዝግጅት** ዙሪያ ነበር ተብሏል። በዚኽም መድረክ ላይ የተገኙት ምክትል አፈ-ጉባኤዋ ወ/ሮ ሎሚ በዶ፣ የምክር ቤቱ የሴቶች ኮከስ አባላት የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማሳደግ በርካታ ሥራዎችን ማከናወኑን አንስተዋል። ከዚያ ባለፈም፣ የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማረጋጥ የሴቶች ኮከስ እስከ አሁን ያከናወናቸውን ተግባራት ውጤት በመመዘን ለቀጣይ ሥራዎች የሚዘጋጅበት ወቅት መሆኑንም አመላክተዋል ተብሏል። የሥልጠኙእው አዘጋጅ የኔዘርላንድ ኢንስቲቲዩት ኦፍ መልቲ ፓርቲ ዲሞክራሲ የአገር ቤት ተወካዩ ዶ.ር. ይነበብ ንጋቱ በበኩላቸው፣ ሴቶች በአንድ አገር ፖለቲካ ውስጥ ትልቅ ሚና እንዳላቸው ጠቅሰው፣ መደመጥ እና ንቁ ተሳትፎ ማድረግ አለባቸው ማለታቸውን ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ጠቅሷል።

በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ወርኃ ኅዳር እንደራሴዎቹ ስለ'ራሳቸው የተወያዩበት ጉዳይ፣ የምክር ቤታቸውን የዚኽ ባጀት ዓመት የሩብ ዓመት የሥራ አፈጻጸም እንደነበር ከምክር ቤታቸው ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል። በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሪፎርም ኮሚቴ፣ **የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት የ2018 ባጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ**ን፣ የጽሕፈት ቤቱ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች፣ የተለያዩ የሥራ ክፍሎች መሪ ሥራ አሥፈፃሚዎች እና የሚመለከታቸው አካላት በተገኙበት አከናውኗል። ሪፖርቱም፣ በስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አሥፈፃሚዋ ወ/ሮ ፈለጉሽ ወርቁ አማካኝነት በዝርዝር ቀርቦ፣ ተጨማሪ ማብራሪያ እና ምላሽ ያሻቸዋል የተባሉ አፈጻጸሞች ተነስተው ውይይት ተደርጎባቸዋልም ተብሏል።

የሪፎርም ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ መለሰ መና፣ በባጀት ዓመቱ የጽሕፈት ቤቱን አሠራር እና ውጤታማነትን የሚያጠናክሩ ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ኹሉም የጽሕፈት ቤት አመራር እና ሠራተኞች በትጋት መሥራት ይገባቸዋል ብለዋል ተብሏል፡፡ የኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶ.ር. አብርሃም በርታ በበኩላቸው፣ በጽሕፈት ቤቱ የተከናወነው የሪፎርም ሥራ በሩብ ዓመቱ ንቁ እና ቅንጅታዊ አንድነትን ያሳየ የሥራ መንፈስ በተለያዩ የጽሕፈት ቤቱ ክፍሎች እንዲታይ ያስቻለ መሆኑን አንስተዋል። በሩብ ዓመቱ በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን እና በተለይ ከጽሕፈት ቤቱ የሪፎርም ሥራ ጋር ተያይዞ ውጤት ለማስመዝገብ የሚያስችሉ የተለያዩ ነባር እና አዳዲስ አደረጃጀቶች በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ሥራን እንዲያከናውኑ የሚያስችሉ መሠረታዊ ሥልጠናዎች መሰጠታቸውን ያነሡት ደግሞ፣ በጽሕፈት ቤቱ የሙያዊ ዘርፍ ምክትል ዋና ጸሐፊው ዶ.ር. ንጉሤ መሸሻ መሆናቸውን ዘገባው ጠቅሷል። በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የመንግስት ዋና ተጠሪ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው አንድነት አድነው በበኩላቸው፣ ኮሚቴው በሚያደርጋቸው ክትትሎች በርካታ መሻሻሎች እንዳሉ አንስተው፣ ኹልጊዜም ሥራዎች በስኬት እንዲጓዙ የሚያስችሉ ችግሮችን እየፈቱ የሚሄዱበት አሠራርን ተከትሎ መሄድ እንደሚገባ ገልፀዋል ተብሏል።



*እንደራሴዎቹ የ2018 ዓ.ም. የሩብ በጀት ዓመት ዕቅዳቸውን ሲገመግሙ፤*

## 7. ኢትዮጵያ ምን ተስማማች?

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ኅዳር ወርን ያሳለፈው፣ አገሪቷ ከአንድ ዓለም ዓቀፍ ተቋም ጋር ያደረገቻቸውን ኹለት የብድር ስምምነቶችንም በማጽደቅ ነበር።

እንደራሴዎቹ በቀዳሚነት ያጸደቁት የብድር ስምምነት፣ **የኢትዮጵያ መንግሥት ከዓለም ዓቀፍ የልማት ማኅበር ጋር፤ ለዘላቂ እና ንጹሕ ኢነርጂ ተደራሽነት ለውጥን ለማፋጠን የተያዘውን ፕሮግራም ማስፈጸሚያ** ነበር። እንደራሴዎቹ በሙሉ ድምጽ ያጸደቁትን ይኽን የ294 ሚሊየን ዶላር የብድር ስምምነት አስመልክቶ የተናገሩት፣ በምክር ቤቱ የመንግስት ተጠሪው የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ፣ የብድር ስምምነቱ የችሮታ ጊዜን ጨምሮ በ31 ዓመታት ውስጥ የሚከፈል መሆኑን ገልጸዋል ተብሏል። እንደራሴዎቹም፣ የስምምነቱን ረቂቅ ዐዋጅ፣ ዐዋጅ ቁጥር 1398/2018 ሲሉ በሙሉ ድምጽ አጽድቀውታል።

የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት በዚያው ዕለት ያጸደቀው ሌላይኛው ረቂቅ ዐዋጅ፣ **የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግሥት ከዚኹ፤ ዓለም ዓቀፍ የልማት ማኅበር ጋር ያደረገው የ20 ሚሊየን ዶላር ከወለድ ነጻ ስምምነት** እንደነበር ከምክር ቤቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል። በዚኹ ስምምነት ዙሪያ ለእንደራሴዎቹ ማብራሪያ የሰጡትም የተከበሩ ዶ.ር. ተስፋዬ በልጅጌ ሲሆኑ፤ እርሳቸውም፣ ብድሩ የስድስት ዓመታት የችሮታ ጊዜን ጨምሮ በ38 ዓመታት ውስጥ የሚከፈል መሆኑን ለምክር ቤቱ አብራርተዋል ተብሏል።

በኢትዮጵያ እና በዓለም ዓቀፍ ልማት ማኅበሩ መካከል የተደረጉት ኹለቱ የብድር ስምምነቶች ኢትዮጵያ እያከናወነች ያለውን የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ለማሳካት ዘርፈ-ብዙ ጥቅሞች እንዳሉት የምክር ቤቱ አባላት መግለጻቸው ተጠቅሷል። የብድር ስምምነቶቹ፣ ኢትዮጵያ ከያዘችው የልማት አቅጣጫ አንፃር ግብርናውን በቴክኖሎጂ በመደገፍ የገጠር ትራንስፎርሜሽን እቅድ ለማሣካት፣ ኢትዮጵያን ወደ አግሮ-ኢንዱስትሪ ለማሸጋገር፣ ከኃይል ምንጭ በተጨማሪ ታዳሽ የኃይል አማራጮችን ለማስፋት፣ የሥራ ዕድል ለመፍጠር፣ የቴክኖሎጂ እውቀት ሽግግር ለማድረግ እና በኹሉም ዘርፍ የበለፀገች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ከፍተኛ ጥቅም እንዳለው የተናገሩት ደግሞ፣ የተከበሩ መለሠ መና ነበሩ ተብሏል። እንደራሴዎቹም፣ ይኽኛውን የብድር ስምምነት ዐዋጅ ቁጥር 1399/ 2018 አድርገው በሙሉ ድምጽ ማጽደቃቸውን ከምክር ቤቱ ያገኘነው መረጃ ይጠቁማል።



*እንደራሴዎቹ ብድሮቹን ሲያጸድቁ፤*

## ፰. ኅዳሩ ሲታጠን

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች፣ በወርኃ ኅዳር አንድ ብሔራዊ ሥርዓትንም ተግብረዋል። በ'የዓመቱ ኅዳር 29 የሚከበረው የብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በዓልን ደመቅ ባለ ኹኔታ እንዳከበሩ መረጃዎቹ ሲያመለክቱ፣ የምክር ቤቱ ከፍተኛ የሥራ ኅላፊዎችም በሥነ-ሥርዓቱ ላይ የተለያዩ መልዕክቶችን አስተላልፈዋል። "ዴሞክራሲያዊ መግባባት ለብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ቃል ለ20ኛ ጊዜ የተከበረውን ይኽንን በዓል አስመልክቶ መልዕክታቸውን ያስተላለፉት፣ የጽሕፈት ቤቱ ዋና ጸሐፊ ተወካይ ከረዩ ባናታ፣ የዜጎችን ብዝሓነትን እና አካታችነትን ማክበር የአገርን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ እድገት ላይ አስተዋጽኦው የጎላ መሆኑን አመላክተዋል ተብሏል። በጽሕፈት ቤቱ በብቃት እና የሠው ሀብት አሥተዳደር ሥራ አሥፈፃሚዋ ወ/ሮ ወርቅነሽ ወጆ አማካኝነት፣ "ዴሞክራሲ እና የፌዴራል ሥርዓት በኢትዮጵያ፦ ተስፋዎች እና ተግዳሮቶች" በሚል ርዕስ የመወያያ ሰነድ መቅረቡም ሲዘገብ፤ አቅራቢዋም፣ የዲሞክራሲን ሥርዓት ለመገንባት በመወያየት፣ በመመካከር እና በመደማመጥ ስሜታዊ ሐሳቦችን በመግታት ችግሮችን በመፍታት ጠንካራ አካታች እና የኔነትን ስሜትን የሚፈጥር አገረ-መንግሥት መገንባት ያስፈልጋል ማለታቸውን የምክር ቤቱ መረጃ ጠቅሷቸዋል። በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ዋና ተጠሪ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው አንድነት አድነው በበኩላቸው፣ አንዱ የሌላውን መብት በማክበር ብዝሓነትን ማስተናገድ እንደሚቻል እና የዲሞክራሲን መርህ ተግባራዊ በማድረግ ብዝሓነትን በማካተት እና በመግባባት አገረ-መንግሥቱን መገንባት እንደሚገባ ገልፀዋል ተብሏል።



*20ኛው የብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በዓል ሲከበር፤*

## 9. ሹመቶች

በዚኽ ዕትም ሽፋን በሰጠነው ኅዳር ወር፣ እንደራሴዎቹ ካከናወኗቸው ተግባራት ሳይጠቀስ የማያልፈው፣ ለተለያዩ የፌደራሉ ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች የሰጧቸው ሹመቶች ናቸው። ኅዳር 25 2018 ዓ.ም. በዋለው የምክር ቤቱ 5ኛ ዓመት 3ኛ መደበኛ ስብሰባ፣ ምክር ቤቱ ሦሥት ሹመቶችን ሰጥቷል። ምክር ቤቱ፣ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ.ር. ዐቢይ አሕመድ የተሾሙትን **የሰላም ሚኒስትር መሀመድ ኢድሪስ፣ የግብርና ሚኒስትሩን አዲሱ አረጋን እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አሥፈፃሚ ሆነው በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተመደቡትን ቢንያም ኤሮን** ሹመት አጽድቋል። ተሿሚዎቹም፣ በምክር ቤቱ ፊት ቀርበው ቃለ መሀላ ፈፅመዋል።



*የግብርና ሚኒስትሩ ሆነው የተሾሙት አዲሱ አረጋ እና የሰላም ሚኒስትር ሆነው የተሾሙት መሀመድ ኢድሪስ፤(ከግራ ወደቀኝ)*



*የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አሥፈፃሚ ሆነው የተሾሙት ቢንያም ኤሮን፤*

## 10. የብሪጅ አጭር ዳሰሳ፦ በብሔር ብሔረ ሰቦች በዓለ ቀን እና ባሻገር ዙሪያ

የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት የጸደቀበት ኅዳር 29 የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን ተብሎ በአገር ዓቀፍ ደረጃ በድምቀት እንዲከበር የተወሰነው፣ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሚያዚያ 21 ቀን 1998 ዓ.ም ባካሄደው ሶስተኛው የምክር ቤት ዘመን አንደኛ አመት ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ ነበር። ውሳኔው የኢትዮጵያ ሕዝቦች መክረው እና ፈቅደው ያጸደቁት ሕገ-መንግሥት ያስገኘላቸውን ጥቅሞች እንዲያስቧቸው፣ መብቶቻቸውን እና ነጻነቶቻቸውን ጠብቀው ማቆየት ብቻ ሳይሆን ‘ርስ በ‘ርስ ማስተዋወቅ እና ማስተሳሰር እንዲችሉ ለማድረግ መሆኑም ያለተጻፈ ደንብ መሆኑ ግልጽ ነው።




የፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን በየዓመቱ ኅዳር 29 ቀን እንዲከበር በዋነኛነት የወሰነው የአገራችን ሕዝቦችም ተመካክረው እና ፈቅደው ያጸደቁት ሕገ-መንግሥት ያስገኘላቸውን ጥቅሞች እንዲያስቧቸው ለማድረግ እና በቀጣይ ማከናወን የሚገባቸውን ተግባሮች ላይም መምከር እንዲችሉ ለማድረግ የታለመ መሆኑም አሌ አይባልም። ከዚህ ቀደም የነበሩትን በዓላት መሪ ቃላት በማስታወስ፣ ይህንኑ የፌደሬሽኑን ግብ ይጠቁማልና፣ አጠር አድርገን ብንጠቅሰው ስዕሉን ሰፋ ያደርግልናል።

### ስያሜዎቹ ሲታወሱ

በአገራችን የመጀመሪያው የብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን፣ በ1999 ዓ.ም. በፌዴሬሽን ምክር ቤት አዘጋጅነት በአዲስ አበባ ሲከበር፣ መሪ ቃሉም “ሕገ-መንግሥታዊ ቃል ኪዳን የአብሮነታችን መገለጫ ነው” የሚል ነበር።

2ኛው በዓል ደግሞ በቀድሞዋ ደቡብ ኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ማዕከል በሆነችው ሀዋሳ ላይ በድምቀት ሲከበር፤ መሪ ቃሉም “ልዩነታችን ውበታችን፣ ውበታችን አንድነታችንና ጥንካሬያችን ነው” በሚል ነበር ።

3ኛው በአዲስ አበባ ከተማ አዘጋጅነት ሲከበር መሪ ቃሉም “ዴሞክራሲያዊ አንድነታችንን በማጠናከር ልማታችንን እናፋጥናለን” የሚል ነበር።

4ኛው በዓል ደግሞ በድሬደዋ አሥተዳደርና አጎራባች ክልሎች (ኦሮሚያ፣ አፋር፣ ኢትዮጵያ ሶማሌ እና ሐረሪ እንዲኹም ድሬደዋ ከተማ አሥተዳደር) በአንድነት አዘጋጅነት፣ በድሬዳዋ በ2002 ዓ.ም. የተከበረ ሲሆን፤ መሪ ቃሉ “መቻቻል ለዴሞክራሲያዊ አንድነት እና ልማት” የሚል ነበር።

5ኛው ከዓለም የፌዴራል ቀን ጋር በማያያዝ በ2003 ዓ.ም. በአዲስ አበባ የተከበረ ሲሆን፣ መሪ ቃሉም “የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች እጅ ለጅ ተያይዘን የአገራችንን ሕዳሴ ወደ ማይቀለበስበት ደረጃ እናደርሳለን” የሚል ነበር።

6ኛው በትግራይ ክልላዊ መንግስት አዘጋጅነት በመቀሌ በ2004 ዓ.ም. ሲከበር፣ መሪ ቃሉ “ሕገ-መንግሥታችን

ለብዝሓነታችን፣ ለአንድነታችን እና ለሕዳሴያችን” የሚል ነበር፡፡

7ኛው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን ደግሞ በአማራ ክልላዊ መንግስት አዘጋጅነት በባሕር ዳር ከተማ በ2005ዓ.ም የተከበረ ሲሆን መሪ ቃሉም “ብዙም አንድም ሆነን በመለስ ራዕይ በሕገ-መንግስታችን ለሕዳሴያችን” የሚል ነበር፡፡

8ኛው ደግሞ በሶማሌ ክልላዊ መንግስት አዘጋጅነት፣ በ2006 ዓ.ም. ጅግጅጋ የተከበረ ሲሆን፣ መሪ ቃሉም “ሕገ-መንግሥታችን ለሕዳሴያችን” የሚል ነበር፡፡

9ኛው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን በዓል ደግሞ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልላዊ መንግስት አዘጋጅነት በአሶሳ ከተማ፣ “በሕገ-መንግሥታችን የደመቀው ኢትዮጵያዊነታችን ለሕዳሴያችን” በሚል መሪ ቃል ተከበሯል።

10ኛው የብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በዓል ደግሞ፣ በጋምቤላ ክልል 2008 ዓ.ም. ላይ የተከበረ ሲሆን፤ መሪ ሀሳቡም ''የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ተሳትፎ ለላቀ እድገት እና ትራንስፎርሜሽን'' የሚል ነበር።

11ኛው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በዓልም እንዲኹ፤ ''ሕገ-መንግሥታችን ለዲሞክራሲያዊ አንድነታችን እና ለሕዳሴያችን'' በሚል መሪ ሀሳብ በ2009 ዓ.ም. በሐረር ተከብሯል።

12ኛው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን፣ "በሕገ-መንግሥታችን የደመቀ ኅብረ-ብሔራዊነታችን ለሕዳሴያችን" በሚል መሪ ሃሳብ በአፋር ዋና ከተማ ሰመራ ተከብሯል።

13ኛው የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓል፣ "በብዝኃነት የደመቀ ኢትዮጵያዊ አንድነት" በሚል መሪ ቃል፣ በዋና ከተማዋ አዲስ አበባ በደመቀ ሁኔታ ተከብሯል፡፡

14ኛው የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት አዘጋጅነት፣ “ሕገ-መንግሥታዊ ቃልኪዳናችን ለዘላቂ ሰላም” በሚል መሪ ቃል እንዲኹ በአዲስ አበባ ከተማ ተከብሯል።

15ኛው የብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን፣ “እኩልነት እና ኅብረ-ብሔራዊ አንድነት ለጋራ ብልፅግና!” በሚል መሪ ቃል በአፋር ክልል በሰመራ ከተማ ተከብሯል፡፡

16ኛው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓል በድሬዳዋ አስተዳደር አዘጋጅነት ኅዳር 29፣ “ወንድማማችነት ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት” በሚል መሪ ቃል ተከብሯል።

17ኛው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ቀን በዓል፣ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ በአፍሪካ ኅብረት አዳራሽ በተለያዩ ፕሮግራሞች፣ "ኅብረ ብሔራዊ አንድነት ለዘላቂ ሰላም" በሚል መሪ ቃል ተከበሯል ፡፡

18ኛው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ቀን፣ በፌዴሬሽን ምክር ቤት አስተባባሪነት እና በሶማሌ ክልል አስተናጋጅነት በጅግጅጋ ከተማ “ብዝኃነት እና እኩልነት ለአገራዊ አንድነት” በሚል መሪ ቃል ተከብሯል።

19ኛው የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ደግሞ፣ "አገራዊ መግባባት ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ቃል በአርባ ምንጭ ከተማ ተከበሯል፡፡

የዘንድሮው 20ኛው የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ቀን ደግሞ፣ በፌዴሬሽን ምክር ቤት አስተባባሪነት እና በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል አስተናጋጅነት በሆሳዕና ከተማ፣ "አገራዊ መግባባት ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት" በሚል መሪ ቃል በዚሁ ወር መከበሩ ይታወሳል።

## ፖለቲካ እና ባህል

በየዓመቱ ኅዳር 29 ቀን የሚከበረው የብሄር ብሔረሰቦች ቀን አሁን በሥራ ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፓብሊክ ህገ መንግሥት የጸደቀበት ቀንን

ምክንያት በማድረግ እንደሆነ ይታወቃል። ይሁን እንጂ በዓሉ ከፖለቲካዊ ዳራው ይልቅ ባህላዊ እንድምታው ጎልቶ እንደሚታይ ከበዓል ዝግጅቱ መረዳት ይቻላል፡፡ የአመለካከት፣ የፍላጎት እና የፖለቲካ አቋም ልዩነቶች በገነኑባቸው አገራት የብሔር ብሔረሰብ ቀንን የመሳሰሉ በዓላት የሰላም እና የእርቅ ዓላማን ለማራመድ ብሎም አገራዊ አንድነትን ለማጠናከር ሊያገለግሉ እንደሚችሉ ብዙ ምሁራን ይገልጻሉ። በቀደመው የኢሕአዴግ ዘመን፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የብሔር ብሔረሰቦችን ቀን እንዲሁ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ እና የሥርዓቱን ተቀባይነት የማጠናከር ዓላማን የሰነቀ ነው ብቻ እንደነበር ይተቻል። ተቺዎቹ እንደሚሉትም፣ በዓሉ የሚወክለው ሥርዓት መሠረታዊ ችግሮች የሚስተዋሉበት ከመሆኑም ባሻገር፤ የዲሞክራሲ እና የሰብዓዊ መብት መርሆች ሊከበሩ ባለመቻላቸው የአገሪቱ ፖለቲካዊ ምኅዳር ከድጥ ወደማጥ በመቆርቆዝ ላይ በነበረባቸው ዓመታት ነበር። በዓሉን አስታከው የሚካሄዱ የአደባባይ ትርዒቶች እና ዓውደ ጥናቶች፣ በተለያዩ ብሔሮች መካከል መከባበርን ለማምጣት፣ የፖለቲካ እኩል ተሳታፊነትን እንዲሁም የምጣኔ ኃብት እኩል ተጠቃሚነት ለማስገኘት የሚያበረክቱት ፋይዳም እንደሚኖር መረዳት ያሻል። አልፍዕም፣ በየዓመቱ የሚከበረው ኅዳር 29 ባህላዊም፣ ፖለቲካዊም አውድ የተላበሰ ነው ይላሉ ፡፡

በኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 8 በኢትዮጵያ ሉዐላዊ የፖለቲካ ሥልጣን ባለቤቶች ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ናቸው በማለት እንደሚደነግግ የሚጠቅሱ ጸሐፍት በበኩላቸው፣ ፖለቲካው የአገሪቱን ኅብረ ብሔራዊነትን እና ብዝሓነትን ለማሳየት የተቀረጸ መሆኑን ያስታውሳሉ። በዚሁ አንቀጽ ላይ ፖለቲካዊ ዓላማ በሚል ያስቀመጠው በሕዝቦች መካከል እኩልነትን እና ወንድማማችነትን እንዲሰፈን ማድረግ በሚል ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ይህም በባህላዊ ትዕይንቶች ጭምር የሚገለጽ መሆኑን ግልጽ ያደርገዋል። በዓሉም ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ የብሔረሰብ ውክልና ባለው የፌዴሬሽን ምክር ቤት አሥፈጻሚነት እየተካሄደ ለመገኘቱ ይህ ማስረገጫ ይሆናል።

የኅዳር 29 የብሔር ብሔረሰቦች በዓልን በመልካም ገጽታው የሚመለከቱት ያሉትን ያህል የዘውግ ፖለቲካ ቅጥያ አድርገው የሚመለከቱም አልታጡም። ያም ቢሆን፣ በዓሉ ብሔር ብሔረሰቦች የአለባበስ እና የአጨፋፈር ቱባ ባህላቸውን ለማስተዋወቅ ዕድል እንደሚፈጥር የሚናገሩ ተሟጋቾች፣ ትዕይንቱ በሕዝቦች መካከል ባህላዊ መገባባትን ለመፍጠር ያስችላል ባይ ናቸው። በተለይ በሙዚቃ እና በዳንስ ዘርፍ ወደ ኪነ ጥበባዊ የኢንዱስትሪ ገበያ ለመግባት መነሻ ሆኖ እያገለገለ ይገኛልም ይላሉ። በርካታ ባህላዊ ድምጻዊያን እና የሙዚቃ ባለሙያዎች ከዚህ በመነደርደር የሙያውን ዘርፍ እንዲቀላቀሉ አስችሏቸዋል ሲሉም የበዓሉን ሁለንተናዊ ፋይዳ ይጠቅሳሉ።

## ቀኑ እና ምክር ቤቱ

ምንም እንኳን፣ የብሔር፣ ብሔረሰቦች ቀን ሲከበር፣ ጉዳዩ በቀጥታ የፌዴሬሽን ምክር ቤትን እንደሚመለከተው ግልጽ ቢሆንም ቅሉ፣ የኢትዮጵያ እንደራሴዎችንም ዋጋ ባላቸው ነጥቦች እንደሚነካቸው አሌ አይባልም።



***የ20ኛው የብሔር ብሔር ብሄረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን በሚከበርበት ወቅት***

በኢትዮጵያ የፌደራሊዝም ሥርዓት ውስጥ የብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ቀን እና የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ያላቸው ተዛምዶ፣ ሕገ-መንግሥታዊ የመብት ባለቤትነት እና የተተግባራዊነት ዝምድና ሊባል ይችላል።

ይኽንንም ቢያንስ በኹለት ዋንኛ ነጥቦች አዛምዶ መጥቀስ የሚቻል ይመስለናል።

- **የሉዓላዊነት ትዕምርት**

በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 8/1 ላይ እንደተጠቀሰው፣ የአገሪቱ ሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤቶች የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ናቸው። ከዚኽ አንጻር ኅዳር 29 ከምክር ቤቱ ጋር ያለው ቁርኝት፣ ብሔር ብሔረ ሰቦች ይኽ ቀን የሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤትነታቸው ትዕምርት መሆኑን የሚያስረግጡበት ዕለት ሲሆን፤ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ደግሞ ሕዝቦች ይኽን ሉዓላዊ ሥልጣናቸውን በተወካዮቻቸው አማካኝነት በተግባር የሚገልጹበት ከፍተኛው የፌዴሬሽኑ የሥልጣን አካል ማድረጉ ነው። ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ባለቤት ሲሆኑ፤ ምክር ቤቱ ደግሞ ያንን ሉዓላዊነታቸውን ማስረገጫ ከፍተኛው የፌዴሬሽኑ ተቋም መሆኑ፣ ትስስሩን የበረታ ያደረገዋል።

- **ሕገ-መንግሥታዊ ውል እና ተቋማዊ ጥበቃ**

የብሔር ብሔረሰቦች ቀን የሚከበረው፣ ሕገ-መንግሥቱ የፀደቀበትን ዕለት መሠረት በማድረግ መሆኑ ይታወቃል። ይኽ ሕገ-መንግሥት ደግሞ፣ በብሔሮች፣ ብሔረ ሰቦች እና ሕዝቦች መካከል የተደረገ የጋራ የፈቃድ ቃል-ኪዳን ወይም አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ ለመፍጠር የተደረገ ጠንካራ የጋርዮሽ ውል ተደርጎ ይወሰዳል። የኅዳር 29 በዓል እና የምክር ቤቱ ኹለተኛው ተዛምዶ ያለውም እዚኹ ነጥብ ላይ ነው፤ የእንደራሴዎቹ ምክር ቤት የተቋቋመው በዚኹ ሕገ-መንግሥታዊ ውል መሠረት ነው። ምክር ቤቱ የሚያወጣቸው ሕግጋት እና የሚወስናቸው ኹሉም ውሳኔዎች በሙሉ በብሔር፣ ብሔረሰቦች ቀን የሚከበሩትን ሕገ-መንግሥታዊ መብቶች (ማለትም እኩልነት፣ ራስን በራስ ማስተዳደር፣ ቋንቋ እና ባህልን ያለጣልቃ ገብነት ማበልጸግ) የሚጠብቁ እና የሚያስፈጽሙ መሆናቸው ላይ ተቋማዊ እርግጠኝነት እንዲኖረው የመገደዱ እውነታ ነው።

## የበዓሉ መሠረት

የበዓሉ መቆሚያ መሠረት፣ የኢፌድሪ ሕገ-መንግሥት መሆኑ ግልጽ ነው። የኢትዮጵያ እንደራሴዎችም፣ ዕለተ-ቀኑን በመንተራስ በተለይም በዚኹ የብሔር፣ ብሔረ ሰቦች እና ሕዝቦች ስየማ ጉዳይ፣ ዳግም ነገሩን የሚያጤኑበት የሚሆንበት ዕድል እንዳለ ብሪጅ ትገነዘባለች። ስለዚህም፣ በስየማዎቹ ዙሪያ ኹለቱን ጫፎች አንስቶ ማለፍ፣ ቢያንስ በዚኹ ዓመት ይጀመራል ተብሎ ለሚጠበቀው የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋንኛ ርዕሰ ጉዳይም ነውና፣ ማንሳቱ ፋይዳ ይኖረዋል ብለን እናምናለን።

የብሔር ብሔረሰቦችን ቀን በየዓመቱ ኅዳር 29 ቀን ማክበር ከተጀመረ እነሆ ዐሥራ ዘጠኝ ዓመታት ሞላው፡፡ ሁሌም ግን፣ የበዓሉ መሠረት በሆነው ሕገ-መንግሥቱ ላይ ስለተቀመጠው እና "እኛ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረ ሰብ እና ሕዝቦች" ስለሚለው አገላለፅ ዛሬም ጥያቄ ሲነሳ ይደምጣል። አንዳንዶች በበኩላቸው፣ "ብሔር፣ ብሔረሰብ እና ሕዝብ" ሦስት ቃላት እንጂ አንድ ትርጉም ብቻ ያለው ሐረግ አይመስልም ባይ ናቸው። እንደነዚህኞቹ ተንታኞች፣ ይህንን በትክክል ለመረዳት በሕገ-መንግሥቱ አርቃቂዎች የተዘጋጀውን አጭር ማብራሪያ ማየት አስፈላጊ ነው። በማብራሪያው ላይ በብሔር፣ ብሔረሰብ እና ሕዝብ መካከል የመጠን እና የስፋት ልዩነት ያለ ቢሆንም ... " እያለ ይቀጥላል። ስለዚህም፣ ልዩነታቸውን በማብራሪያው ላይ ባይዘረዝርም በደፈናው "የመጠንና ስፋት" ልዩነት እንዳላቸው አስቀምጧል።

ከዚህ አኳያ ሌሎች አስተያይት ሰጪዎች እንደሚሉት፣ ብሔር አንድ ትርጉም ሲኖረው፤ ብሔረሰብም ደግሞ ሌላ ትርጉም፤ ሕዝብም እንደዚኹ ሌላ ትርጉም ቢኖረውም፣ ሕገ-መንግሥታችን ግን ሦሥቱን ቃላት አንድ ላይ ሰብስቦ የኢትዮጵያን ነገር ቻል ብሎ 'ስታንሊናዊ' ብያኔ ይሰጠዋል ሲሉ ወቀሳቸውን ያሰማሉ። በእርግጥም በሕገ-መንግሥቱ ላይ ለሦሥቱም አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም ተሰጥቷቸዋል፡፡ ይኸውም፡-

"ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት ቋንቋ ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑና የሥነ-ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክአ ምድር የሚኖሩ ናቸው" (አንቀጽ 39/5) የሚል ነው። ይህ የትርጓሜ ሐሳብ ደግሞ፣ በተለይም የሕገ-መንግሥቱ ብዙኋኑ አርቃቂዎች ርዕዮተ-ዓለማዊ ዳራ ከሆነው ስታሊኒዝም ጋር መተሳሰሩን መዘንጋት አያሻም። ነገሩን ለማስረገጥም፣ ጆሴፍ ስታሊን ከጻፈው እና እኒኹ ብዙኋኑ ያልናቸው የተማሪ ንቅናቄው አባላት የነበሩት አርቃቂዎች በፖለቲካዊ የመብቃት ዘመናቸው ካነበቡት፣ "Marxism and the National Question" ከሚለው እ.አ.አ. በ1913 ከታተመው ጹሑፉ ቀጣይ ማሰላሰያ አርሾ ያቀብለን ዘንድ ኹለት አንቀጾችን እንጥቀስ፤

*"A nation is a historically constituted, stable community of people, formed on the basis of a common language, territory, economic life and psychological make up manifested in a common culture" ("ብሔር ማለት በታሪክ ሂደት ውስጥ የተገነባ፣ የተረጋጋ ማኅበረሰብ ሲሆን፤ የተመሠረተውም በጋራ ቋንቋ፣ ግዛት፣ ኢኮኖሚያዊ መስተጋብር እና በጋራ ባህል ውስጥ በሚገለጥ ሥነ-ልቦናዊ መዋቅር ላይ ነው። ") (307)*

*"It must be emphasized that none of the above characteristics taken separately is sufficient to define a nation. More than that, it is sufficient for a single one of these characteristics to be lacking and the nation ceases to be a nation." ("ከላይ ከተጠቀሱት መለዮዎች መካከል አንዳቸውም ቢሆኑ በነጠላ አንድን ብሔር ለመበየን በቂ እንዳልሆኑ አጽንኦት ሊሰጠው ይገባል። ከዚህም በላይ፣ ከ'ነዚህ መለዮዎች መካከል አንዱ እንኳን ቢጎድል፣ ያ ብሔር ብሔር መሆኑ ያበቃለታል።" (ዝኒ ከማኹ)*

ከስታሊን ይህን መሰሉ ብያኔ በመለስ፣ ከአገር ቤት ደግሞ አንድ ማንጸሪያ መዝገበ-ቃላትን ብንጠቅስ፣ ነገሩን ሰፋ ሳያደርግልን አይቀርም። በዘመኑ በነበሩ የበቁ የተባሉ ግራ ዘመም ምሁራን የተዘጋጀው፣ 'የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት' ብሔረሰብን ሲፈታው፦

*"ብሔረሰብ ከደም አንድነት ይልቅ የተመሠረተው በክልል፣ በቋንቋና በባህል አንድነት ላይ ነው። ብሔረሰብ የነገድ ከፍተኛ ደረጃ የሆነ የብዙ ነገዶች ውህደት ውጤት ነው። . . . የዕድገት ሂደት ከሚጠይቀው አንጻር ሰፋ ያሉ የኢኮኖሚ ግንኙነቶችን በመፍጠር እነዚህን ልዩነቶች የሚያስቀር የብሔረሰብ ከፍተኛ ደረጃ ብሔር ነው። "(206)*

ለብሔር ደግሞ ቀጣዩን ፍቺ ይሰጣል፦

*". . . አንድ ብሔር በመጀመሪያ ደረጃ የሚለየው ባሉት የወል ቁሳዊ የኑሮ ሁኔታዎች ነው። በአንድ መልክአምድራዊ ክልል ውስጥ መኖር፣ በኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች መተሳሰር፣ በአንድ ቋንቋ መጠቀም፣ በጋራ ታሪካዊ ሂደት ውስጥ የወል ሥነ ልቦናዊ ገጽታዎችና ባህላዊ አመለካከቶች መከሰት የብሔር መሠረቶች ናቸው። " (ዝኒ ከማኹ፣ 213)*

ያም ሆነ ይህ፣ ይኸው ፍቺ ትንሽም ቢሆን እርማት ያስፈልገዋል የሚሉ ድምጾች በበኩላቸው፣ አንድ የማኅበረ ሳይንስ ርዕሰ-ጉዳይን ያጣቅሳሉ፤ ይኸውም፣ የጋራ ጠባይ ለግለሰብ እንጂ ማኅበራዊ ቡድን ለሆኑት ብሔር አልያም ለብሔረሰብ የምንጠቀምበትን አግባብ በማጠየቅ፣ የአንድ ብሔር ጠባይ እንደምን ያለ ነው? ምንስ ነው ያልሆነው? ብያኔዎቹን በያኙስ ማን ነው? ምንስ ላይ ተቀዋ? ሲሉም መጠይቃዊ ሐሳብ ይሰነዝራሉ።

ነገረ-ጉዳዩን በሌላ ገጽ ስንመለከተው ደግሞ ሌሎች ነጥቦችን ልናነሳ ይቻለናል። ምሳያችንም፣

ፌዴሬሽኑን የመሰረቱት ክልሎች ሕገ-መንግስት ይዘታዊ ጉዳይ ነው። አስቀድሞ፣ የክልሎቹን ሕገ-መንግስቶች ሕገ-መንግሥት ብለን መጥራታችን ከፌዴሬሽኑ መቆሚያ ከሆነው ሕገ-መንግሥት ጋር ማስተያየት አይሆንምን? የሚለውን ሥነ-እውቀታዊ ጥርጣሬን አለማንሳት የሚቻል አይመስልም። ከዚያ ባለፈ፣ የክልሎቹ ሕገ-መንግስቶች ላይ ትርጉም የተሰጠው በአጠቃላይ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በማለት ሳይሆን የብሔሩን አልያም በክልሉ ውስጥ የሚኖሩ ብሔሮችን ስም በመግለጽ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ሊጠቀስ የሚችል የአተረጓጎም ልዩነት እንደማይታይባቸው መረዳት ይቻላል። ከዚህ አንጻር ነገሩን ስናጤነው፣ ብሔረሰብ የሚለውን በአንድ አካባቢ የሰፈረ የሚለውን ወስደን ለመረዳት ስንሞክር፣ እንደ የአይሁድ የተለያየ የዓለም ክፍል ላይ እየኖሩ ተመሳሳይ ቋንቋ መናገሩ እና አንድ አይነት ባህል መጋራቱ ብቻ ብሔረሰብ ቢያሰኘውም፣ በአንድ አካባቢ በተለይታነት አለመስፈሩ ግን፣ የእኛን የብሔረሰብ አልያም የሕዝብ ብያኔ ፈንገጥ ያለ ሳያደርገው አልቀረም። ከዚህ የማኅበረሰባዊ ጥናት አኳያ ለመመልከት ገፋ አድርገን ከሄድን፣ የተለያዩ አካባቢዎች የሚኖር ነገር ግን ተመሳሳይ ባህል ያላቸውን መሰል ማኅበራዊ ቡድኖችን ብሔር ወደማለት እንገፋለን። ሕዝብ የሚለውን ስንወስድም፣ ከቀለም እና ከቋንቋ ባሻገር አንድን ሕዝብ አንድ የሚያደርገው አንድ ሉአላዊ አገር መኖሩን የሚያስታውሱን በጉዳዩ ላይ የተጻፉ መዛግብት፣ ሕገ-መንግሥታችን እነዚህን ለያይቶ አላስቀመጠም ሲሉም ቅሬታቸውን ያነሳሉ።

የዚኽን ቅሬታ ፈጣሪ ጉዳይ ከየት መጤነት ከሚያስታውሱን የሕገ-መንግሥቱ አርቃቂዎች አንዱ የነበሩት ዶ.ር. ነጋሶ ጊዳዳ፣ በወቅቱ ነገሩን በቅጡ እንዳላሰቡበት ያስታውሳሉ። "መጀመሪያ ሕገ-መንግስቱ ውስጥ መግባት ያለባቸው ምንድን ናቸው ብለን 73 ጥያቄዎች አዘጋጀንና ጥያቄዎቹ በምርጫ መልክ ተዘጋጅተው ወደ ሕዝቡ ወረዱ” ሲሉ ትውስታቸውን የጻፉት የኤፌድሪው የመጀመሪያ ኘሬዝደንት፣ ጥያቄዎቹ ላይ ሕዝቡ ከተወያየ በኋላ በየቀበሌው የተሰጠው ሐሳብ በ‘የክልሉ ከተሰበሰበ በኋላ ጥያቄዎቹን በሕገ-መንግሥቱ አንቀፆች መሰረት እንደከፋፈሏቸው ያስታውሳሉ። “ከዚያም አንቀፆቹ ሲከፋፈሉ 106 ሆኑ” የሚሉት ነጋሶ፣ ነገር ግን ይኽ የሕገ-መንግሥቱ አገላለፅ መብራራት እንዳለበት መጠየቁን አያስታውሱም። የሕገ-መንግሥት አርቃቂ ጉባኤውን በሊቀ መንበርነት የመሩት አቶ ክፍሌ ወዳጆ በበኩላቸው፣ "ሕገ-መንግሥቱ በሚረቀቅበት ወቅት በሰፊው ተቃውሞ ከነበረባቸው ክፍሎች መካከል መግቢያው አንዱ ነበር።” ይላሉ። ኹለቱም የወቅቱ አርቃቂዎች ግን፣ ሕገ-መንግሥቱ መነሻም መድረሻም በመሆን ያገለገለው ስታንሊናዊነት ባይ ናቸው።

እንደ ብሪጅ እምነትም፣ ገዢው ብልጽግና ፓርቲ ጭምር፣ ከሕገ-መንግሥቱ እንዲሻሻል የሚፈልጋቸውን የተወሰኑ አንቀጾች ለአገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ማስገባቱ፣ እነኚኽን መሰል አከራካሪ ጉዳዮችን ለመፍታት ምቹ ኹኔታ ይፈጥራል።

## ፍካሬ ዘ እንደራሴ

“እንደራሴ” የሚለው ንባበ-ቃል በኢትዮጵያ ጥንታዊ እና ዘመናዊ የፖለቲካ ተዋስዖ እና የሥነ-መንግሥት ታሪክ ውስጥ ግዝፈት የነሳ ፍካሬያዊ ንባበ-ቃል ነው። የቃሉ ከየት መጥነት እና ፍካሬም፣ በአጠቃሎ መልኩ ይኽን መሰል ፍቺዎች ነበሩት/አሉትም።

ንባበ-ቃሉ የተገኘው “እንደ” እና “ራሴ” ከሚሉ የኹለት ቃላት ጥምረት ነው። “እንደ”፦ መስያ፣ ፈንታን ወይም ምትክን ሲያመለክት፤ “ራሴ”፦ ራስ ጠሪውን ማንነት አልያም ባለቤቱን-ሲፈከርም ባለሥልጣኑን ያነጽራል። በአማሪያዊ ፍቺውም፣ “እንደ እኔ” ወይም “እኔን ሆኖ” ማለት ነው ይሏል። በኢትዮጵያ ሥነ-መንግሥት ታሪክ “እንደራሴ” የሚለው ማዕረግነቱን ሲያጣቅስ፣ በተለያዩ ዘመናት የተለያየ ማኅበረ-ፖለቲካዊ ትርጓሜ ነበረው፤ ለማሳያ፦

ሀ- የንጉሠ ነገሥቱ ተወካይ (በፈረንጅ አፍ- Regent እንዲሉ)፦ በንጉሣዊው ሥርዓት ዘመን ንጉሠ ነገሥቱ በአንዳች ምክንያት (ለዐቅመ-መንበር ባለመድረስ፣ በሕመም ወይም በሌላ ምክንያት) አገረ-መንግሥቱን መምራት ካልቻሉ፣ ሙሉ ሥልጣን ተሰጥቶት አገሪቱን የሚያሥተዳድረው ሰው “ቢትወደድ-እንደራሴ” ይባል ነበር።

ለ- የአካባቢ ወይም የክፍለ-ሀገር ገዢነት፦ ንጉሠ ነገሥቱ በየክፍለ ሀገራቱ ‘ራሳቸው ዘወትር መገኘት ስለማይችሉ፣ በ‘ርሳቸው ስም የሚፈርዱ እና የሚያሥተዳድሩ ተወካዮቻቸውን “እንደራሴ” ይሏቸዋል፤ ይኽም የንጉሡ ምሉዕ ተወካይነትን ይሰጣል።

ሐ-የሕዝብ እንደራሴነት፦የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ከመጣ ወዲኽ ግን ቃሉ አዲስ ፍካሬ ያዘ። ሕዝቡ በ‘ራሱ ፈንታ ሆኖ በምክር ቤት እንዲመክርለት እና ውሳኔም እንዲሰጥለት የሚመርጣቸው ሰዎች “የሕዝብ እንደራሴዎች” መባል ጀመሩ። የዚኽ ፍካሬም፣ “ሕዝቡን ሆኖ የሚሠራ”፣ “ምስለ-ሕዝብ” አልያም “የሕዝቡ ተወካይ” የሚል ትርጓሜን አሰጠው።

ዛሬ “ተወካይ” (በምዕራቡ የምክር ቤት ታሪክ ጅማሮ-Representative-እንዲሉ) ከሚለው ቃል ጋር መሳ ለመሳ ሆኖ ያገለግላል። ሆኖም “እንደራሴ” የሚለው ቃል ከውክልና ባለፈ፣ የወከለውን አካል ሙሉ ክብር እና ማንነታዊ ተዛምዶ ይዞ የሚገኝ ክብደት ያለው ፖለቲካዊ እና ማኅበረ-ባህላዊ ፍካሬ አለው።

## የብሪጅ አፈካከር

ተቋማችን ብሪጅ፣ የአማርኛን ሰዋስው ደንብ ጠብቃ፣ ይኽንን ቃል ከኋለኛው ወደዚኽ ዘመን አናጥቃ በመፈከር ተጠቅማለች። አስቀድመን ሊቃውንቱ ያስቀመጡትን እንጥቀስ፤ ደስታ ተክለ ወልድ፣ እንደ ራሴ፣ እኔን ሆኖ፣ የእኔን ሥልጣን ይዞ የሚሠራ ብለው ሲፈቱት፤ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ በፈንታ፣ በምትክ የሚቆም ሲሉት፤ ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጸው በተራቸው፣ ተለዋጭ፣ ተወካይ፣ ባለሙሉ ሥልጣን የሚል ፍቺ ይሰጡታል። ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀልም ቢሆኑ፣ አንድ ሰው በራሱ ስም ሳይሆን በሌላው ስም ተገኝቶ የሕግ ተግባራትን ሲያከናውን እንደራሴ መባሉን ያነሳሉ። እነዚኽ ዋቢዎች እንደሚያሳዩት፣ ቃሉ በመጀመሪያ ለነገሥታት ተወካዮች ብቻ ይሠራበት የነበረ ሲሆን፣ ኋላ ለሕዝብ ተወካዮች እንዲሠራበት የተደረገው የሕዝቡን ልዕልና ለመግለጽ ውለዋል፤ አለፍ ሲልም፣ ተወካዩ ሕዝቡን ሆኖ ይገኛል፤ እንደ ሕዝቡ ሆኖ ይጠራል የሚለውን ፍካሬ ይሰጣሉ።

በዚኽ አግባብ፣ “እንደራሴ” ስንል፦ አንድም ራስ የሚለውን የኢትዮጵያ ፌዴሬሽን ከቆመበት ‘የራስን ዕድል በራስ የመወሰን’ ሕገ-መንግሥታዊ ነባር መርህ ጋር አናጽረን ፈክረነዋል። ይኽ ማለት፣ በዚኽ መርህ ውስጥ ያለው ‘ራስ’፣ የሚለው ትርጉም የሚጠቅልላቸውን ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች፣ በ “እንደራሴ” ውስጥ ያለውን ‘ራሴ’ን ለመፍታት ፍካሬያዊ ትርጓሜን ተጠቅመናል። ከዚያ ባለፈም፣ በቀደመው ዘመን መራጩ ንጉሠ ነገሥቱ እንደሆነው ሁሉ፣ በዚኽኛው የእኛው ዘመን ሕዝብ ነውና፣ “እንደራሴ” ስንል፦ እንደ መረጠው ሕዝብ፣ ብሔረሰብ አልያም ብሔር የሆነ በሚል ፍቺ መጠቀማችንን ልብ ይሏል። በዘመናዊው የምርጫ ሥርዓት ስናነጽረውም፣ መራጩ ግለሰብ እንደራሴውን ‘ተናገር በከንፈሬ፣ ተቀመጥ በመንበሬ’ ሲል፣ በነገረ-ሕይወቱ ይወስንለት ዘንድ ወደ ምክር ቤቱ መርጦ ይልከዋል። የመረጠውም እንደራሱ ካልሆነለት፣ ምስለ እኔነቱን ሊነጥቀው መቻሉን ያስረግጣል።

የ“እንደራሴ” ንባበ-ቃል፣ ምንም እንኳን የመጀመሪያው የኢትዮጵያ የእንደራሴዎች ምክር ቤት ሲቋቋም፣ የምክር ቤቱ የሥራ ቋንቋ በዘመኑ ብሔራዊ ቋንቋ የነበረው አማርኛ ብቻ ቢሆንም ቅሉ፣ ንባበ-ቃሉ ግን በሌሎቹ የአገራችን የብሔር ብሔረ ሰቦች ቋንቋዎች ውስጥም መገኘቱን ልብ ይሏል፤ ለማሳያ፦ በሲዳማ- amaalete mina፣ በአፋን ኦሮሞ-Bakka bu’aa፣ በትግሪኛ- ከማይ፣ በወላይተኛ Kal Atiya/Taga ton መባሉን ያስታውሷል።

**ከራስ ውርድ፦**

“በእነዚኽ ወርኃዊ የእንደራሴዎቹ ጥቅንሮች ውስጥ ያሉት ኹሉም የገጸ-ሰብ እና የገጸ-መስኮች ምስሎች የተገኙት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ይፋዊ የመረጃ ምንጮች ነው፤ እንዲኹም፣ ኹሉም ቁጥራዊ ዘገባዎች የተወሰዱትም ከዚኽ ምንጭ ነው። ዳሰሳዊ ምልከታዎቹ፣ አጠቃሎዎች እና ተያያዥ ትንታኔዎቹ የተቋማችን ናቸው።”

# እንደራሴ

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል፡፡

**BRIDGE** Research & Innovation for Democratic Governance and Enhanced Peace

+251 115 57 74 96

+251 911 86 12 34

research@bridge-et.org

https://bridge-et.org/

150096, Addis Ababa, Ethiopia.

Kazanchis, across the main gate of UNECA, SA Building, 9th Floor, Office No. 5, Addis Ababa.